አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


# የ**8**ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን በማስተማር ለሚሰጥ የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ


አማረ ግርማ


**ጥቅምት፣ 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

# የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋ ጥናት፤ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ

አማረ ግርማ

አማካሪ፡ ታደሰ ሲባሞ (ዶ/ር)

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥቅምት፣ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ፤

ስም ______________________________________ፊርማ _____________ቀን_____________

የውስጥ ፈታኝ

ስም_____________________________________ ፊርማ________________ ቀን____________

የውጭ ፈታኝ

ስም_____________________________________ ፊርማ________________ ቀን____________

## የምርምር ጥራትና ወጥነት ማረጋገጫ

ይህ ጥናት "የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች" በሚል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም በሌላ አካል ያልተሰራ ወጥ የምርምር ስራ መሆኑንና በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ድርሳናት በተገቢው ዋቢ የተደረጉ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- አማረ ግርማ

ፊርማ፡-____________

ቀን፡- ______________

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም ለዚህ ስራ መሳካት ምክንያት የሆነኝንና የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ጥናቱ ከርዕስ መረጣው ጀምሮ አሁን የደረሰበትን ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስተያየት በመስጠት፣ በማረምና በማቃናት ላደረጉልኝ እገዛ ዶክተር ታደሰ ሲባሞን ከልብ አመሰግናለሁ። እንዲሁም በክፍል ውስጥ በነበረኝ የመማር ሂደት ስለምርምር ሙያዊ እውቀታቸውን ላከፈሉኝ የትምህርት ክፍሉ መምህራን ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

በሶዶ ከተማ አስተዳደር ሊጋባ በየነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አብዮት ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራ እና በጥናቱ ለተሳተፉ የ2015 ዓ.ም በስምንተኛ በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ለዚህ ጥናት መሳካት ላበረከቱልኝ አስተዋጽኦ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጽሁፍ ስራዬ ኮምፒውተራቸውን በመስጠት ላበረከቱልኝ እገዛ ለአቶ አብርሃም ታደስ እና ባለቤታቸው እንዲሁም ለዶክተር ወንዳፍራሽ ደበበ ባለቤታቸው ምስጋናዬ ትልቅ ነው።

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ሂደት ከጎኔ ላልተለየችኝ ባለቤቴ አልማዝ ተሚሪ እና ለእህቴ ራሔል ግርማ  ምስጋናዬ የከበረ ነው።

ማውጫ

ርዕስ
ገጽ


ምስጋና ........ v

አጠቃሎ ........ viii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2

1.3. የጥናቱ አላማዎች ........ 4

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች ........ 4

1.5. የጥናቱ ገደብ ........ 4

ምዕራፍ ሁለት ........ 6

ክለሳ ድርሳናት ........ 6

2.1. የንግግር ክሂል ምንነት ........ 6

2.2. የንግግር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት ........ 11

2.3. የንግግር ክሂልን ክፍል ውስጥ እንዴት እናስተምራለን? ........ 13

2.4. ንግግር የሚቀርብባቸው አላማዎች ........ 14

2.5. የመናገር ክሂልን አቀራረብ ተግባራት ........ 15

2.5.1. የቅድመ ንግግር ተግባራት ........ 15

2.5.2. የንግግር ጊዜ ተግባራት ........ 17

2.5.3. የድህረ ንግግር ተግባራት ........ 18

2.6. የንግግር ክሂል መመዘኛዎች ........ 18

2.7. የንግግር አይነቶች ........ 18

2.7.1. ተራክቧዊ ንግግር ........ 19

2.7.2. መደበኛ ንግግር ........ 19

2.7.3. አውድ ተኮር ንግግር ........ 19

2.8. የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ የትግበራ ዘዴዎች ........ 20

2.9. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ........ 24

2.9.1. ትውውቅ ........ 24

2.9.2. ልምምድ ........................................................................ 25
2.9.3. አፍልቆት ........................................................................ 25
2.10. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................................................ 25
ምዕራፍ ሶስት ........................................................................ 28
የጥናቱ ዘዴዎች ........................................................................ 29
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........................................................................ 29
3.2. የጥናቱ ናሙናዎች አመራረጥ ........................................................................ 29
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................................................ 31
3.3.1. የጽሁፍ መጠይቅ ........................................................................ 31
3.3.2. የክፍል ምልከታ ........................................................................ 32
3.4. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ........................................................................ 32
ምዕራፍ አራት ........................................................................ 33
የመረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........................................................................ 33
4.1. ከጽሁፍ መጠይቅ እና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................................ 33
4.1.1. ........................................ የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርና 33
4.1.2. ...... የተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የልምምድ ሂደት የመረጃዎች ትንተና ........................................................................ 42
4.1.3 የተማሪዎች በክፍል ውስጥየመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት መምህራን የልምምድ አውድ አዘግጅቶና የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀም ........................................................................ 51
4.2. የውጤት ማብራሪያ ........................................................................ 55
ምዕራፍ አምስት ........................................................................ 57
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ ........................................................................ 57
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................ 57
5.2. አስተያየት ........................................................................ 57
ዋቢ መጻሕፍት ........................................................................ 59
አባሪ ........................................................................ 65

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፈተሽ ነው። ጥናቱም ለመረጃ አሰባሰቡና አተናተኑ መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ (Mixed approach) ነው። ይህ ጥናት የተካሄደው በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሊጋባ በየነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አብዮት ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም በ 8ኛ ክፍል በመማር ያሉ ተማሪዎች እና የደረጃው መምህራን ተሳትፈዋል። ከእነዚህም ተማሪች እና መምህራን መረጃዎች የተሰበሰቡት ከክፍል ምልከታ፣ ለተማሪዎችና ለመምህራን ከተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ ነው። የትንተናውም ውጤት በመቶኛ ተሰልቶ በገለጻ ስልት ተብራርቷል። የትንተናው ውጤቱም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለንግግር ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ትኩረት ያልሰጡ መሆናቸው፣ በተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የተሰጣቸው ትብብራዊነት በተማሪዎች መካከል እንዲታይ ያለማድረጋቸው፣ ተማሪዎችን ለማነቃቃት መሰራት የነበረባቸው ተግባራት መረሳታቸው፣ የአውድ ዝግጅት ትኩረት የይድረስ መሆኑ፣ ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርቱ እኩል ያለማሳተፍ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ያለማድረግ እና የሚመረጡ የንግግር ማስተማሪያ ርዕሶች ከተማሪዎች የእለት ተእለት ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር የማጣጣም ስራ አለመሰራቱን ተመላክቷል። ስለሆነም፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የታዩ ክፍተቶች ከመምህራን ትኩረት ማነስ የመጡ ናቸዉ።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋዎች ትምህርት ሁለት መሠረታዊ አላማዎችን በማያያዝ የሚቀርብ የትምህርት ዘርፍ ነው። እነዚህም መሠረታዊ ዓላማዎች ክሂሎትን ማሳደግና የዕውቀት ዘርፎችን ማስገኘት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ፤ ትምህርት ሚኒስተር (2004) "የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ ማንበብና የመጻፍ ክህሎትን ማጎልበት እንዲሁም ስነ-ጽሁፍንና የስነ-ልሳን መሰረታዊ እውቀቶችን ማዳበር መሆናቸው ይታወቃል" ብለዋል።

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ስለቋንቋው ዕውቀት እንዲኖራቸውና አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን በማዳበርና በማጎልበት በታላሚው ቋንቋ ጥሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህም እንዲሆን የተለያዩ ክንውኖችን መፈጸም አስፈላጊ ነው። ከእነዚህ ክንውኖች ሃሳብን ወይም ስሜትን በመናገር መግለጽ ዋነኛው ተግባር ነው። መናገርም ስሜት ያፈለቀውን፣ ዓይን የተመለከተውን ወይም ከንባብና ከማዳመጥ የተቀሰመውን ግብዓት መነሻ በማድረግ ሀሳብን ሥርዓት ባለው መንገድ ለሌላ ወገን ለማስደመጥ መሞከር ነው። ይህ አገላለፅ ደግሞ መናገር ከቋንቋ ክሂሎች አንዱና በአፍአዊ የክሂል ስር የሚጠቃለል እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው። በተጨማሪም መናገር ከመልዕክት ጋር መያያዝ እንደሚኖርበትና የአድማጬንም መኖር የግድ የሚል ቋንቋው የሚፈቅደውንና ተቀባይነት ያለውን አሰላለፍ የሚጠይቅ መሆኑን ለማስተዋል አዳጋች አይመስልም።

Ur (1996) እንደገለጹት፣ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መናገር ግንባር ቀደምትነት አለው። አንድ ሰው አንድን ቋንቋ ያውቃል ሲባል ቋንቋውን መናገር ይችላል እንደማለት ነው። ይህም ሌሎች በንግግር ጥላ ስር ሊታቀፉ እንደሚችሉ ይጠቁማል። በተጨማሪም ንግግር በቃላት አጠቃቀሙ፣ በአውዳዊነቱ፣ በተለያየ ሰዋስው ገፅታው (የቃላት ድግግሞሽ፣ የተቆራረጡ የሚመስሉ ሃሳቦች የመያዙ፣ ቆምታን የሚያካትቱ አገላለፆች ያሉበት መሆኑ ወዘተ) ከፅሕፈት ይለየዋል።

በታላሚው ቋንቋ የተማሪዎችን ተግባቦት ለማጎልበት የመከታተል ፍላጎትና ተነሳሽነት ለመፍጠር በትምህርቱ በክፍለ ጊዜ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመፍጠርና በማመቻቸት መምህራን ከፍተኛ ሚና አላቸው። በሚፈጠርላቸው ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ከክፍል ውጪ የንግግር ባህሪያትን በመለየት በተሳካ ሁኔታ ሃሳባቸውን መግለጽ ይችላሉ።

የማፍለቂያ ክሂሎች የሚባሉት መፃፍና መናገር ናቸው። ንግግር የሰው ልጅ መግባቢያ በሆነ ቋንቋ ሃሳብን የመግለፅና መልዕክትን የማስተላለፍ ተግባር ነው። ፅህፈት ደግሞ የንግግር ወኪል ነው። ፅህፈት ሃሳብን ቋሚና እይታው በሆነ ትእምርት ቀረፃ ለማቆየት የሚያስችል ፣ በቦታና በጊዜ የማይወሰን ህያው ሆኖ የሚቆይ ምልክት ነው። የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን በሰጡትን ብያኔ መሰረት ልዩነታቸውና ተመሳሳሎ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በአሁኑ ወቅት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመናገር ክሂል አሰጣጥ ጎላ ያለ ችግር ያለበት እና መምህራን ይህንን ክሂል ትኩረት በመስጠት እያስተማሩ እንደይደሉ ጥናቶች ያመለክታሉ (መንግስቱ፣ 1997)። የዚህም ጥናት አቅራቢ ማስተማር ላይ በቆዩበት ጊዜ መምህራን በአጠቃላይ ለአማርኛ ቋንቋ ብሎም ለመናገር ክሂል የሚመደቡት ክፍለ-ጊዜ በጣም አነስተኛ ከመሆኑም ሌላ ይህን ክሂል መምህራን አቅደውና ዓላማ ነድፈው ሳይሆን ተለምዷዊ በሆነ መንገድ እንደሚተገብሩ አስተውሏል።

ስለሆነም፣ ይህ ጥናት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሰስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኩራል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቋንቋ ትምህርት በተለይም ክህሎችን ትኩረት ሰጥቶ በክፍል ውስጥ ማስተማር አያሌ ጠቀሜታዎች አሉት (McDonought and Shaw, 1993 and Byme, 1981:108):: እነዚህም ቋንቋውን ተፈጥሯዊ በሆነ መቼት ለመማር አጋጣሚን መፍጠር፣ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ሆነው ልዩ ልዩ ተግባራትን እንዲሠሩ ማበረታታት፣ ከክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ተማሪዎች ትርጉም ያለው ሥራና እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ እና ነባራዊነት ያለውን ቋንቋ እንዲጠቀሙ ማገዝ ናቸው። እንዲሁም፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ከማጠናከርም ሆነ ከማላላት አኳያ ቋንቋ ከፍተኛ ሚና እንዳለው የሚታመን ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች በማህበራዊ

ግንኙነት ውስጥ ብቁ ተሳታፊ ሆነው ሐሳባቸውን ለሌላ ወገን ከማስተላለፍ ረገድ ከፍተኛ ረብ አለው። ይሁን እንጂ እንደ Nguyen (2021) ገለጻ፣ ተማሪዎች ጠንካራ የተግባቦት ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አኳያ በትምህርት ቤቶቻችን ተግባራዊ የሚደረገው የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበር ደካማ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳይንሳዊ በሆነ በመንገድ ማየት የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ነው።

ሌላው አጥኚው ባስተማራቸውና አሁንም በሚያስተምርበት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አካባቢ አብዘኛዎች መምህራን ተማሪዎቹ ወደ ፊት በስፋት የሚሳተፉበትን ማህበራዊ ህይወት መሠረት ያደረጉ የንግግር መለማመጃዎችን በማሰናዳት ሲያስተምሩ አይታዩም። እንደዚሁም በርካታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ክንውኖች ማለትም ራስን መግለጽ (Talking about one self) ፣ ምስለትና የሚና ጨዋታ (Simulation & Role Play)፣ ታሪክን ማዋቀር (Story Construction)፣ ውይይት (Discussion) እና ክርክር (Debating) በታለሚ ቋንቋ ሲፈፅሙ አይታዩም። ከዚህ በመነሳት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትኩረት ተሰጥቶት መቅረብ አለመቅረቡን የመፈተሽ አስፈላጊነት ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው።

ስለሆነም፣ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምን እንደሚመሰል መገምገም የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው።

1. የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ይመስላል?
2. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርትን አተገባበር ወቅት የአቀራረብ ሂደቱ ምን ይመስላል?
3. በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ?

## 1.3. የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ዋና ዓላማ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የንግግር ክሂልን የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መፈተሽ ነው። ከዚህ ዋና ዓላማ በመነሳት ጥናቱ ያሉት ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉ ናቸው።

1. የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ፤
2. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የአቀራረብ ሂደቱ ምን እንደሚመስል መፈተሽ፤
3. በንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማራቸውን መመርመር፤

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በተሳካ ሁኔታ ተጠንቶ ውጤቱ ሲገኝ በመጀመሪያ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ምን እንደሚመስል ከተፈተሸ በኋላ እንዴት መቅረብ እንዳለበት ለመጠቆም፣ በመቀጠል ተማሪዎች የመናገር ክሂል ሲማሩ ሊገኝ የሚችለዉን ጠቀሜታ ለመግለፅ፤ በተጨማሪም የረጅምና የአጭር ጊዜ የመምህራን ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ክፍሎች የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብን ትኩረት ሰጥተው እንዲያሰለጥኑ ለማመልከት ይረዳል።

ስለዚህ ይህ ጥናት፡-

- መምህራንና ተማሪዎች ዉጤታማ የንግግር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለወደፊቱ እንዲጠቀሙ ያመላካታል፤
- መምህራንና ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚያግዙ ተግባራትን ለማወቅ ያግዛል፤
- በዚህ ጥናት ዙሪያ በቀጣይ ለማጥናት ለሚፈልጉት መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሊጋባ በየነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አብዮት ጮራ አንደኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት ናቸዉ፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ጥናቱ ያተኮረው በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን፣ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አልተመለከተም፡፡ እንዲሁም ከንግግር ክሂል ውጭ ሌሎች ክሂሎችን አልተመለከተም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ማጣቀሻነት መፃህፍት እና ጥናቶች የተዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡ በስፋት ለማየት የተሞከረው የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ንደፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች ናቸው። በዚህ መሰረት የንግግር ክሂል ምንነት፣ ዓይነት፣ የንግግር ክሂልን የማስተማር አስፈላጊነት፣ የንግግር ክሂል አተገባበር፣ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ብልሀት፣ የንግግር ክሂል መማሪያ ተግባራት፣ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች እና የንግግር ክሂልን ማስተማሪያ መርሆዎች በሚመለከት በስፋት ተዳሰዋል።

## 2.1. የንግግር ክሂል ምንነት


ዓይን የተመለከተውን፣ በማዳመጥና በንባብ የተገኘውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሀሳብን ለሌላ ወገን ስርአት ባለው መንገድ ማስተላለፍ መቻል ነው። Thanyalak (2012: 1) እንደሚያስረዱት፣ የንግግር ክሂል ለቃላዊ ተግባቦት ከሚያስፈልጉ የቋንቋ ችሎታዎች አንድ ሆኖ ከመማሪያ ክፍል ውጭም ሆነ በመማርያ ክፍል ውስጥ ራስን ከሌሎች ጋር ለማግባባት የሚያስችል መሳሪያ ነው። በተጨማሪም ሌሎች ክሂሎች እንደ ማንበብንና መፃፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመማር መሰረት ሆኖ ያገለግላል። አክለውም ምሁሩ በንግግር ወቅት ትክክለኛ መልእክት ለማስተላለፍ ቃላትን፣ እርባታዎችን፣ የቋንቋውን ሥርዓት በትክክል ለይቶ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል።

ስለዚህ ከምሁሩ ንድፈ-ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ንግግር በሰው ልጆች የመግባባት ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያለው ሲሆን፣ ሀሳብን ወይም መልእክትን ወደ ተቀባይ ለማድረስ የቋንቋውን ሥርዓት በትክክል ማወቅ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ይህ ከላይ የተቀመጠው የምሁሩ ብያኔ በአንፃራዊ መልኩ ሌሎች የመስኩ ምሁራን ይቃወሙታል። በንግግር የተሟላ መልእክት ለማስተላለፍ የሰዋስው እውቀት ወይም የቋንቋውን ስርዓት ብቻ ማወቅ ሳይሆን ማህበረ-ባህላዊ ዐውድ(Socio-cultural Competence)፣ የዲስኩር ደንብ (Discourse Competence) እና የብልሀቶች እውቀትን (Strategic Competence) ማወቅ ያስፈልጋል

(ማረው እና ሰፉ፣1999)። ስለዚህ አጥኚው ከዘርፉ ምሁራን አስታራቂ ንድፈ ሀሳብ መውሰድ የቻለው ንግግር ለማካሄድ የቋንቋው ስርዓት፣ የዱስኩር ደንብ፣ የብልሀት እውቀት እና ማህበረ-ባህላዊ አውድ ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ነው።

ይህንን ንድፈ-ሃሳብ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ስዕላዊ ሞዴል እንመልከት።


ስዕላዊ ሞዳል አንድ፤




ምንጭ፡- (ማረው እና ሠፉ፣ 1999፣84)


ከላይ ከቀረበው ስእላዊ ሞዴል መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ላይ የመናገር ክህሎታቸውን ለማዳበር ተግባቦታዊ ችሎታን የሚያሳድጉ እንደ ማህበረ-ባህላዊ አውድ፣ የድስኩር ደንቦች እና ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት በተለያየ አውድ መጠቀም ሲችሉ ነው። ተማሪዎች በተግባቦታዊ ችሎታ ወቅት የብልሃት እውቀቶችን ሲጠቀሙ በርካታ ግብአቶችን (Inputs) ለመሰብሰብና የሚያውቁትንም የንግግር ቋንቋ ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። በተጨማሪም በንግግር ወቅት አንደበተ ርቱዕ (Fluencey) እንዲሆኑና ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ እንዲጠቀሙ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው (ማረው፣1999) ። ይህን ንድፈ-ሃሳብ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ስዕላዊ ሞዳል በአስረጅነት ቀርበዋል።

ስዕላዊ ሞዴል ሁለት፡- የተግባቦት ችሎታ ገፅታዎች ከማረው እና ሰፉ (1999፣88) የተወሰደ



የንግግር ክሂል በግንባር መገናኘትን የሚጠይቅ በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚካሄድ የሁለትዮሽ ተሳትፎ የሚታይበት ክሂል ነው (ፅጌ፣ 1994፤ ተስፋዬ ፣ 1981፤ ማረው፣ 1998 እና በድሉ፣ 1996)። ይህንን ሃሳብ በመደገፍ Byrne (1992) እንደገለጹት፣ የንግግር ክሂል ከቋንቋ ክሂሎች አንደ ሆኖ የተለያዩ ጉዳዮች በውስጡ እንደሚያጠቃልል ያስረዳሉ። እነሱም እንደሚከተለው ከስር በስዕል ቀርበዋል።

ስዕላዊ ሞዴል ሦስት፡- የንግግር አለባውያን




ከ**Byrne (1992: 10)** የተወሰደ

ከላይ ከተቀመጠው ስዕል እንደምንረዳው የንግግር ክሂል የአድማጭን ምላሽ የሚፈልግ ክሂል ሲሆን ክሂሉን ለማከናወን በተናጋሪ እና በአድማጭ መካከል ምላሽ እና መነሳሳት የሚያስፈልግ መሆኑን ነው። በተፈጥራዊው ቃላዊ የመግባባት ሂደትም ተናጋሪው የንግግሩ ጀማሪ ቢሆንም የንግግሩ ሂደት ግን የተናጋሪውና የአድማጩን የጋራ ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ ነው። ይህ ማለት ተናጋሪው የተናገረውን አስመልክቶ ከአድማጭ ምላሽ ይፈልጋል። ምላሹ በየንግግሩ ጣልቃ እንደ አስፈላጊነቱ የሚቀርብ ነው፤ ምክንያቱም ተናጋሪው በተናገረው ላይ ከአድማጭ ያገኘውን ምላሽ ተናጋሪው ምን ያህል መልእክቱ እያስተላለፈ እንደሆነ፣ቀሪው ንግግሩን በምን መልክ እና ምን ላይ በማተኮር ማቅረብ እንዳለበት እንዲገነዘበው ያደርጋል። በመሆኑም ንግግር በተናጋሪ እና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ንግግር ዕውቀትን፣ ፍላጎትን ፣ አመለካከትን ፣ ግንዛቤን፣ስሜትን ወዘተ ለሌላ ሰው መግለጫ ነው። ክሂሉ ሲተገበርም በንግግሩ ውስጥ አምስት ክፍሎች ተጠቃለው ይገኛሉ። እነሱም፡- መልእክት አፍላቂ (Source)፣ የሚተላለፈው መልእክት (Message)፣ መልእክት የሚተላለፍበት መንገድ (channel) ማስተላለፊያው (Medium) እና መልእክት ተቀባይ

(Receiver) ናቸው (Richard, 2008)። ስለዚህ ንግግር ስሜታችንና ፍላጎታችንን በቃላት አማካኝነት ለመግለፅ የሚያስችል መልእክትን ማመንጨት፣ማገናዘብንና ማሰብን የሚያጠቃልል፣ በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን ተግባቦታዊ ሂደት መሆኑን መረዳት ይገባል። በተጨማሪ በመረጃ ልውውጥ ተግባር (Transactional function) አንድ መረጃ ወደ ተፈለገው አካል ለማስተላለፍ የሚያስችል ነው (Wallce,etal; 2004 & Nunan,1989)። በአጠቃላይ ንግግር ተራን በመጠበቅ የሚከናወን አድማጭ እና ተናጋሪን ገፅ ለገፅ ለማገናኘት የሚያስችል መግባቢያ ነው።

ንግግር በተፈጥሯዊ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ሂደትም ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ ከቤተሰብና ከአከባቢ የሚማሩት የክሂል አይነት ነው። ንግግር ለተግባቦታዊ አገልገሎት ሲውልም የትክክለኛነት እና የርቱዕነት ባህሪያትን ሊያሟላ ይገባል (Bygate, 2001; Harmer, 1991; Pahuja, 2001; Littlewood, 1981; Atkins & Nuru 1995; ማረው እና ሰፉ፣1999)።

የንግግር የትክክለኛነት ባህርይው ከድምፆች አጠራር፣ ከቃላት አመራረጥ እና አሰዳደር ጋር ሲያያዝ፣ የርቱእነት ባህርይው ደግሞ የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ መልእክትን ያለመሰናክል በአንደበተ ስል ትነት ከመግለፅ ጋር ይዛመዳል (ማረው እና ሰፉ፣1999)። ስለዚህ ተማሪዎች ባገኙት አጋጣሚ የንግግር ክሂል እንዲያዳብሩ መምህራን ማበረታታት አለባቸው። ይህም ሊሆን የሚችለው በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የንግግር ክንዋኔዎች ከትክክለኛነት (Accuracey) ይልቅ በርቱዕነት (fluency) ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ነው። ምክንያቱም የርቱዕነት ክንዋኔዎች የበለጠ በተግባራዊ የንግግር ልምምድ ላይ ያተኩራሉ። በዚህ ምክንያት የርቱዕነትን ባህሪ ማዳበር ተማሪዎች ደፋር ስለሚያደርጋቸው በቋንቋው የበለጠ እንዲለማመዱ ዕድል ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም በጊዜ ሂደት በታላሚው ቋንቋ በትክክል የመጠቀም ችሎታን እንዲያዳብሩ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ከዚህ የምንረዳው የንግግር ክሂል የአንድ የቋንቋ ውስጣዊ መዋቅር ማለትም የሰዋስውና የንበት ስርዓት ጠንቅቆ በመረዳት፣ ፍርሀትን እና ጭንቀትን በማስወገድ ፍሰትን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፍ ችሎታን የሚጠይቅ መሆኑን ነው።

የንግግር ክሂል በጊዜ፣ በአውድ፣ በቦታ፣ ተወስኖ የሚከናወን የክሂል አይነት ነው (Brown &yule, 1983; Dornyei, 2001; Brown, 2007; Sandra, 2002 & Burns,

2006)። ከዚህ ንድፈ ሃሳብ የምንረዳዉ ንግግር በጣም ውሱን በሆነ ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደምንናገር?፣ ምን እንደምንናገር?፣ ለማን እንደምንናገር እና መቼ እንደምንናገር ወዘተ አገናዝበን መልእክት የምናስተላለፍበት የመግባቢያ መንገድ ነው። ሆኖም ግን የምሁራኑ ብያኔ የራሱ የሆነ ክፍተት እንዳለው ምሁራኑ ያምናሉ። ምክንያቱም አንድ ተናጋሪ በተሰጠው አጭር ጊዜ ውስጥ መልእክቱን ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ ከመፈለግ የተነሳ የሰዋስው ስህተት፣ የቃላት ግድፈት ፣የሃሳብ መንዛዛት፣ ፍሰት አልባ በመሆን ንግግሩን እንደሚያቀርብ ካለው ሞያዊ የማስተማር ልምድ ለመገንዘብ ችሏል።

ንግግር በቋንቋ አማካኝነት ሃሳብን በቃል መግለፅ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል። ሀሳብ በንግግር በሚገለፅበት ወቅት መታየት የሚገባቸውና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛ የአረፍተ ነገር አሳካክ መግለፅና የሚገለፀው ሀሳብ በንግግሩ ወቅት ከሚታየው አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተደጋገፈና የተጣጣመ መሆን የሚሉት ናቸው (Richard, 2008)። በቋንቋ አማካኝነት ሀሳቡን በንግግር የሚገልፅ ሰው የሚያሳየው አካላዊ እንቅስቃሴ(የእጅ እንቅስቃሴ፣ በፊት ላይ የሚታዩ ገፅታዎች) ከሚያተኩርበት የንግግሩ ፍሬ ሃሳብ የሚነበብ መሆን አለበት። በአጠቃላይ ንግግር ድምፃዊ ቅንብሩ ብቻ ሳይሆን የፊት ሁኔታና የሰውነት እንቅስቃሴም የማይለየው ክሂል መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

ንግግር ሃሳብን የማደራጀት፣ አሳማኝ ነጥቦችን የመዘርዘር፣ ተገቢ ቃላትን የመጠቀም ችሎታዎችን ይጠይቃል (Cameron, 2001)። ይህን ሃሳብ በተመለከተ ማረው (1998፣139) ሲያስረዳ "የመናገር ክሂል ሊዳብር የሚችለው ህጎችን በማስተማር ወይም በመንገር ሳይሆን እንደማንኛውም ክሂል በተግባራዊ ተሳትፎ ብቻ ነው። ተማሪዎች እየፃፉ የመፃፍ ክሂላቸውን እንደሚያዳብሩ ሁሉ እየተናገሩም የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፤" ይላሉ።

ስለዚህ ከምሁሩ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የተማሪዎች የንግግር ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ የተለያዩ አውዶች ክፍል ውስጥ በማቅረብ ንግግርን በተግባር የሚለማመዱበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚገባ ነው።

በንግግር አማካይነት ሀሳብን የማስተላለፍና የመቀበል ሂደት ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ለዚህም ነው የንግግር ክሂል የሰው ልጅ ህልውና ከሚመሰረትባቸው

መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛ ነው የሚባለው። የንግግር ክሂል የሁለት ችሎታዎች (ማህበራዊና ሥነ-ልሳናዊ) ጥምረት ውጤት ነው። ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋውን መዋቅራዊ ክፍልና ማህበራዊ አጠቃቀም አጣምሮ ማለማመድ ያስፈልጋል። ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት እንዳለው ሁሉ ማህበራዊ አጠቃቀም ስርዓትም አለው። ማህበራዊ ስርአቱ በመዋቅራዊ ስርዓቱ ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል (ማረው፣1998 ፣139) ።

ከምሁሩ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ቃላዊ በሆነ መልኩ በንግግር ስንግባባ የንግግር ችሎታችን የሚለካው የቋንቋውን የአወቃቀር ስርአት ጠብቀን መናገር በመቻላችን ብቻ አይደለም፤ይልቁንስ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው ህብረተሰብ በቋንቋው ሲናገር እንዴት ይናገራል?፣ ማን? ለማን? ምን ይናገራል?፣ወዘተ የሚሉትን ለይቶ በማወቅም ጭምር ነው። ወጣቶች ከወጣቶች፣ ሴቶች ከሴቶች፣ ሴቶች ከወንዶች እና ወጣቶች ከሽማግሌዎች ወዘተ… እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ አነጋገራቸውስ ምን ይመስላል? የሚለውን በመለየት በንግግር ተግባቦት ጊዜ መግለፅ ሲችሉ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው፣ የቋንቋውን ተጠቃሚ እንደሚለውና እንደሚጠቀምበት አድርገው ሃሳባቸውን መግለፅ ብሎም በሚገባ መግባባት እንዲችሉ ሁለቱንም በጥምረት በተቻለ መጠን ክፍል ውስጥ ቢማሩ እና በተግባር ቢለማመዱ ተመራጭ ይሆናል። ስለዚህ ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል፣ ልምድና እውቀት መሰረት በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲፈጥሩና ማህበራዊ ግንኙነታቸውንም እንዲያጠናክሩ መስተጋብራዊ ተግባርን (Interactional function) በክፍል ውስጥ ሊመቻችላቸው ይገባል።

## 2.2. የንግግር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት

የንግግር ክሂል ትምህርት ለተማሪዎች ክፍል ውስጥ ማስተማር ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለምንም መደናገር በመናገር ማስተላለፍ እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን ዕውቀት እና ክህሎት እንዲጨብጡ ለማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ሳይፈሩ እና ሳያፍሩ በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራኖቻቸው ፊት ሀሳባቸውን በትክክል መግለፅ የሚያስችላቸውን ችሎታ አግኝተው በማህበራዊ ህይወታቸው የሚፈልጉትን ጉዳይ በንግግር ማስተላለፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። በድሉ (2007፡87) የመናገር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ እንደሚከተለው አቅርበውታል።

*አብዛኞቹ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በኃላ ያለ ህይወታቸው ያለ ምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ። በራስ ያለ መተማመን፣ አይነአፋርነት መልእክትን በምክንያት እና ውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋውን ስርዓት ያለመጠበቅ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማርዋናአላማም እነዚህ ንዑሳን ክሂሎች በማዳበርተማሪዎች ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።*

Harmer (1991) እንደገለጹት፣ የመናገር ክሂልን ክፍል ውስጥ ማስተማር አስፈላጊ የሚሆነው ተማሪዎች ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፣ ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ ሀሳብን በተጠየቃዊ ቅደም ተከተል ማቅረብን እንዲለማመዱ፣ ግላዊ አመለካከታቸውን በንግግር ነፃ ሆነው እንዲገልፁ፣ አስተያየቶችን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ እና ኢ-መደበኛ የአነጋገር ስልቶችን አስወግደው መደበኛ የአነጋገር ስልት እንዲጠቀሙ ለማድረግ ነው። ከምሁሩ አገላለፅ መረዳት የሚቻለው የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ ማስተማር አስፈላጊነቱ፣ ተማሪዎች ንበቱ የተስተካከለ ቋንቋ በመጠቀም በልበሙሉነት፣ በራስ መተማመን እና በድፍረት ሀሳባቸውን ከሰዎች ፊት ቀርበው መግለፅ እንዲችሉ ለማስቻል ነው።

እንደ Harmer (2007:123) ገለፃ፣ ደግሞ መናገር የምናስተምርበት እና ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የምንፈልግበትን ሦስት ምክንያቶች አሉ። እነሱም፡-

- ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የመናገር ክሂል ተግባራት ለመምህሩ ሆነ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ምን ያህል ጥሩ እንደሰሩ፣ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑና ምን አይነት የቋንቋ ችግር እንዳጋጠማቸው ስለሚለዩበት፣
- የመናገር ክሂል ተግባራት የልምምድ ዕድሎችን ማለትም ለእውኑ ዓለም ንግግር የሚያገለግል የልምምድ ዕድል በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፣
- ተማሪዎች በአእምሯቸው ያከማቹትን የቋንቋ እውቀት የመገልገል አቅምን ስለሚፈጥሩ ያለ ምንም ጭንቀት በጥሩ ሁኔታ የመናገር ችሎታቸውን ስለሚያሳድግ ንግግርን ክፍል ውስጥ እናስተምራለን።

በአጠቃላይ የመናገር ክሂል ክፍል ውስጥ ማስተማር የተለያዩ ማህበራዊና ትምህርታዊ ፋይዳዎች አሉት (ማረው እና ሰፋ፣1999)። ፋይዳዎቹም፣ በርካታ የቋንቋ ዕውቀቶችን ለመቅሰም፣ ዕለታዊ

ተግባራትን በተረጋጋ መንፈስ ለማከናወን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለመፍጠር፣ ራስን በሙያና በንግድ ተግባር ለማሻሻል እና መረጃን ለማስተላለፍ ይጠቅማል።

## 2.3. የንግግር ክሂልን ክፍል ውስጥ እንዴት እናስተምራለን?

ተማሪዎች ንግግርን ሊማሩ የሚችለት ሲናገሩ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ንግግርን የሚለማመዱባቸውን የተለያዩ የክፍል ውስጥ ክንዋኔዎችን በሥርዓት ማደራጀት ያስፈልጋል። እነዚህን የክፍል ውስጥ ክንዋኔዎች የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ያገናዘቡ፣ እንዲሁም የተለያየ አቀራረብ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን የተማሪዎቹ ተሳትፎ እና የመማር ተነሳሽነት ስለሚቀንስ የመናገር ችሎታቸውን ሊያዳብሩ አይችሉም (ማረው፣1998) ።

የመናገር ልምምድ በተለያዩ መንገዶች በክፍል ውስጥ ማስተማር ይቻላል፤ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹ፡- ተማሪዎች በመኖርያ አካባቢያቸው፣ በቤተሰባቸው፣ በትምህርት ቤታቸው ዙሪያ፣ ስለሚፈፀሙ ክንውኖችና ስለሚታዩ ነገሮች የቃል ገለፃ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ የተለያዩ ጭውውቶችንና ድራማዎችን እንዲሰሩ ማቀናጀት፣ የተለያዩ ተረቶችን እንዲተርቱ፣ ቀልዶችን እንዲናገሩ፣ የቃለ መጠየቅ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁና እንዲመልሱ፣ የቡድን ዝማሬ እንዲያሰሙ፣ የብጤ ውይይት እና ጭውውት እንዲያደርጉ፣ የተለያዩ ሰዎችን የንግግር ንባብ፣ የመድረክ አመራር በቴፕ በማስደመጥ አስመስለው እንዲያቀርቡ፣ በአከባቢያቸው የሚፈፀሙ ባህላዊና ልማዳዊ ስርአቶችን በቡድን ወይም በግል ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ ተጠቃሽ ናቸው (Richard, 2008; Sandra, 2002 & Burns, 2006)።

መምህራን የመናገር ክሂል ክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ፍላጎትና የእውቀት ዳራ ተስማሚ የሆኑ የአቀራረብ ብልሀቶችን ተከትለው ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የአቀራረብ ብልሀቶቹም :-

- በጭውውት ማስተማር፡- ጭውውት የመናገር ክሂልን ለማዳበር ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው። ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው በተመረጡ ቅንጫቢዎች በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር ዕውነተኛ የንግግር ዐውድን ይፈጥራል።
- ቃላዊ ሪፖርት በማቅረብ፡- ተማሪዎች ያነበቡትን፣ ያዳመጡትንና ያዩትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለፅ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው።

* ቃለ መጠይቅ በማድረግ፡- ተማሪዎች አንድን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው በቃለ-መጠይቅ አማካኝነት ከሰዎች መረጃ የሚሰበስቡበትና ያገኙትን መረጃ አቀነባብረው በክፍል ውስጥ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው።
* በስዕል አማካኝነት፡- በሚቀርበው ሥዕል መሰረት ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲወያዩና የግል አመለካከታቸው እንዲገልፁለማድረግ የሚቻልበት የአቀራረብ ብልሀት ነው።
* በጥያቄ አማካኝነት፡- የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ወይም ለትምህርቱ የተመረጠውን ቅንጫቢ መሰረት በማድረግ የተለያዩ አነጋጋሪ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲናገሩ የሚያስችል ነው።

ጥያቄዎቹ መፍትሔ የሚሹ፣ የሚያከራክሩና ምናባዊ ጉልበትን (power of imagination) የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ (በድሉ፣ 1996፣ 65-68)።

## 2.4. ንግግር የሚቀርብባቸው አላማዎች

አንድ ተናጋሪ ሊናገር የፈለገውንና የወሰነበት ጉዳይ ብቻ መርጦና አስቦበት ያቀርባል። በዚህም የሚናገረው የአድማጮቹን ይሁንታና ተቀባይነት ከማግኘት አንፃር እያሰበ ሊሆን ይችላል። በንግግር ሰው ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ ምኞቱን መግለፅ ይችላል ሲባል እንዲሁ በባዶ ሳይሆን ጥሩ የመቀበል ችሎታ ሲኖር ነው። በዚህ መሰረት ሊተላለፍ እንደተፈለገው መልዕክት ንግግር የሚቀርብባቸው ዓላማዎች ብዙ ቢሆንም በዋነኛነት ሦስት ናቸው። እነሱም ለማዝናናት፣ ለማሳወቅ እና ለማሳመን የሚደረጉ ንግግሮች ናቸው (ፅጌ፣1994)።

ለተዝናኖት የሚቀርብ ንግግር የመጀመሪያው ሲሆን፣ ተናጋሪው ለማዝናናት አስቦ ከተነሳ ከአድማጮች የሚጠበቅ ልዩ ልዩ ምላሽ ይኖራል፤ ሳቅ፣ ጭብጨባ፣ ፉጨት የመሳሰለት ናቸው። ይህ የሚገኘው ደግሞ ተናጋሪው የማሳቅና የማስጨብጨብ ችሎታ ሲኖረው ነው። ለተዝናኖት የሚቀርብ ንግግር ተቀዳሚ አላማው ማዝናናት እንደ መሆኑ ተናጋሪው ለቋንቋው ውበት ሊጨነቅ ይገባል። የአድማጩን ስሜት የሚነኩ ለዛና ውበት ያላቸው አገላለፆችን መጠቀም ያስፈልጋል። ታዲያ ከላይ እንደተጠቀሰው በዚሁ ሳቢያ ተፈላጊ የሆኑ መልእክቶችና ቁምነገሮች ሊተላለፉበት እንደሚችል ማወቅ ያሻል። አብዛኛው ጊዜ ለተዝናኖት የሚቀርብ ንግግር አድማጭ መንፈሱ ዘና እያለ ስለሚያዳምጠው ያለ መርሳት እድለ ሰፊ ሊሆን ስለሚችል ተመራጭ የመልእክት

ማስተላለፊያ መንገድ ሆኖ ያገለግላላል። በዚህ ንግግርም ተረቶች፣ ቀልዶች፣ ምሳሌዎችና አባባሎች ማጀቢያ በመሆን ያገለግላል።

ሁለተኛው ለማሳወቅ የሚቀርብ ንግግር ነው። የዚህ ንግግር ዋና አላማ አድማጮች እንዲያውቁት፣ እንዲዘጋጁበት፣ እንዲጠነቀቁበት የሚፈልገውን ጉዳይ ማሳወቅ ነው።

ተናጋሪው ለቋንቋው ውበት መጨነቅ የለበትም፤ በተስተካከለ ቋንቋ ንግግሩን ማቅረቡ ተገቢ ነው። ይህን ዓይነቱን ንግግር የሚያቀርብ ሰው አድማጩን ሊገባው በሚችል መንገድ የማቅረብ ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ሁኔታውን በምሳሌ እና መረጃ አስደግፎ መልእክት የማስተላለፍ ልምድም ይጠይቃል።

ሶስተኛው ለማሳመን የሚቀርብ ንግግር ሲሆን፣ አድማጩን አሳምኖ ልክ በተናጋሪው ቦታ እንዲሆን ማስቻል ነው። ተናጋሪው ስነ-ልቦናዊ የሆኑ ሁኔታዎችን ሳይቀር በመጠቀም የአድማጩን ሃሳብ እስከ ማስለወጥ ድረስ ይሄዳል። በተለያዩ ማሕበራዊና ግላዊ ተፅዕኖዎች ሳቢያ አንዳንድ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ የተሳሳተና ግትር አቋም ሊይዙ ይችላሉ። ስለዚህ ይህንን ቀደም ሲል የታወቀውን የግለሰቡን አቋም በማወቅ ንግግሩ ይዘጋጃል ማለት ነው።

## 2.5. የመናገር ክሂልን አቀራረብ ተግባራት

የንግግር ክሂል የተለያዩ ንኡሳን ተግባራትን የያዘ ሂደት እንጂ በአንድ ውስን ጊዜ የሚከናወን ነጠላ ተግባር አይደለም።ይህን ሃሳብ በተመለከተ ማረው (1998) እና በድሉ (1996) ጥሩ ንግግር ቅደመ ዝግጅትን እንደሚጠይቅ ይገለፃል። ስለዚህ ንግግር በሚቀርብበት ጊዜና ከንግግሩም በኋላ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ተግባራት አሉ። እነዚህም ተግባራት የቅድመ ንግግር፣ የንግግር ጊዜ እና የድህረ ንግግር ተግባራት ተብለው በሦስት ይከፈላሉ (በድሉ ፣1996)።

### 2.5.1. የቅድመ ንግግር ተግባራት

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ላይ ከመሳተፋቸው በፊት አስቀድመው ሊያከናውኗቸው የሚገቡ የቅድመ-ንግግር ተግባራት አሉ። ከእነዚህም መካከል ንግግር የሚደረግበትን ርእሰ ጉዳይ መወሰን ወይም መምረጥ፣ በተመረጠው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ንግግር የሚደረግበትን አላማ ማወቅ፣ አድማጮን መወሰን፣ ዋናዋና

ነጥቦችን በማሳታወሻ ማስፈር፣ የተሰበሰቡትን ንድፈ ሃሳቦች በአስተዋፅኦ መልክ መንደፍና ንግግሩ ለአድማጭ ከማቅረብ በፊት ልምምድ ማድረግ፣ ወዘተ. የመሳሰለት ተጠቃሽ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹን ከስር በዝርዝር እንመለከታቸዋለን ።

የንግግር ርዕስ መምረጥ፡- ንግግር የሚደረግበት ርዕስ አስቀድሞ በሌላ አካል የማይወሰን ከሆነ የንግግራችን ርዕስ መምረጥ ያለብን ራሳችን ነን። የንግግር ርዕስ ስንመርጥም በተቻለ መጠን ጠቃሚነት፣ወቅታዊነትና መስህብነት ያለውን እየለየን ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም ጠቃሚነት፣ ወቅታዊነትና መስህብነት በጎደለው ርዕስ የአድማጮን ጆሮ ማግኘት አይቻልምና፤ በዚህ ረገድ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል (Baygte, 2001)። ከጠቃሚነት፣ ከወቅታዊነትና ከመስህብነት አንፃር ተገናዝቦ ርዕሱ በጥንቃቄ ከተመረጠ በኋላ ተከታዩ ተግባር ርዕሱን መወሰንና ማጥበብ ነው።

የንግግር ርዕስ መወሰን ወይም ማጥበብ፡- አንድ ተናጋሪ ከጠቃሚነት፣ ከወቅታዊነት ከመስህብነት አንፃር እየተገናዘበ የሚናገርበትን ርዕስ ከመረጠ በኃላ ተከታዩ ተግባር የተመረጠውን ርእስ በመወሰንና በማጥበብ ላይ ያተኩራል። ርዕሱ ሲወሰንና ሲጠብም ለንግግሩ የተመደበለት የጊዜ ገደብ ጭምር ግምት ውስጥ እየገባ ነው። በወጉ ተወስኖ የቀረበ ርዕስ የተናጋሪውን መነሻና መድረሻ ማመልከት ይችላል፤ መነሳት እና መቅረት የሚገባቸውን ነጥቦችም ለመለየት ያግዛል (Harmer፣1991) ።

የንግግሩን ዓላማ ግልፅ ማድረግ፡- አንድ ተናጋሪ ስለምን መናገር እንደሚፈልግ ወይም ስለምን መናገር እንደሚጠበቅበት መለየት እንዳለበት ሁሉ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ ለምን መናገር እንዲስፈለገው በቅድሚያ ማወቅ ይኖርበታል። ይህንን መለየትና ማወቅ ሲችል ብቻ ነው የንግግሩን ዓላማ ለአድማጭ ማድረስ የሚቻለው። ይህ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ግን የታቀደውን ንግግር በተገቢው መንገድ አድማጭ ዘንድ ማድረስ አይቻልም።

የአድማጮችን ማንነት መለየት፡- ተናጋሪ፣ የአድማጮችን ማንነት በቅድሚያ ማወቅ ይኖርበታል። የአድማጮች ማንነት በትክክል የተረዳ ተናጋሪ፣ ከአድማጮቹ ዕድሜ ፣ ዕውቀት፣ ልምድና ችሎታ ጋር የተገናዘበ ንግግር በማቅረብ ዓላማውን በቀላሉ ያሳካል፤ የአድማጮችን ዕድሜ፣ ዕውቀት፣ ልምድና ችሎታ ያላገናዘበ ተናጋሪ ግን ውጤት ሊያገኝ አይችልም ።

ንግግር በሚደረግበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ መረጃ ማሰባሰብ፦ መረጃ የአንድ የተዋጣለት ንግግር የጀርባ አጥንት ነው። በተለይ ለየት ባለ ወቅታዊ መረጃዎች ላይ ንግግርን እንዲመረኮዝ ማድረግ የበለጠ ተቀባይነት ያስገኛል። በመሆኑም አንድ ተናጋሪ ተፈላጊ መረጃዎች፣ መፃህፍት፣ ሰነድችንና ጥናታዊ ዘገባዎችን፣ ወዘተ. በማገላበጥ ማሰባሰብ ይኖርበታል። ከዚህም ጎን ለጎን የሚመለከታቸው ባለሙያዎችን በማነጋገርም መረጃ ማግኘት እንደሚቻል መዘንጋት የለበትም።

አስተዋፅኦ መንደፍ፦ በንግግር ሂደት ውስጥ የሚካተቱት መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡ በኃላ ተከታዩ ተግባር የሚሆነው መረጃዎቹን አሰባስቦ ቢጋር ወይም አስተዋፅኦ የመንደፍ ጉዳይ ነው። ቢጋሩ ወይም አስተዋፅኦው ተናጋሪው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚያነሳቸውን ቁምነገሮች ከመጠቆሙ በተጨማሪ የአቀራረብ ቅድም ተከላቸውን ጭምር ለማሳየት ይረዳል።

መለማመድ፦ አንድ ተናጋሪ ርዕስ መርጦ፣ አጥብቦና አስተዋፅኦ ነድፎ ከጨረሰ በኃላ ጊዜ ወስዶ በተደጋጋሚ መለማመድ ይኖርበታል።ለሚያደርገው ልምምድ ያግዙት ዘንድም የተለያዩ ስልቶችን ሊጠቀም ይገባል። ስልቶችም፣ የራስን ንግግር በመቅረፀ-ድምፅ ቀርፆ ማዳመጥ ፣ ከጓድኞቹ ፊት ቆሞ ማስታወሻውን እየተመለከቱ መለማመድ፣ ጭር ያለ ቦታ በመምረጥ ለብቻ መለማመድ፣ ከመስታዋት ፊት ቆሞ በግል እንቅስቃሴን በመቆጣጠር መለማመድ፣ ወዘተ. የመሳሰለት ናቸው (Baygate, 2002ከተጠቀሱት የመለማመጃ መንገዶች አንዱን መርጦ ለተማሪዎች በሚገባ መለማመድ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ልምምድ በራስ የመተማመን ስሜትን በከፍተኛ ደረጃ ይገነባል። ይሁን እንጂ የልምምድ ግብ ሽምደዳ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

### 2.5.2. የንግግር ጊዜ ተግባራት

ተማሪዎች ቅድመ ንግግር ተግባራት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ንግግር ተግባር የሚገቡ ሲሆን በንግግር ሂደት ላይ እያለ ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ። ከተግባራቱ መካከል፣

ርዕሱን ለአድማጮች በሚገባ ማስተዋወቅ፣ የንግግሩ አላማ በአጭሩ መግለፅ ፣ የአድማጭን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ፣ አድማጭን በአይን መቃኘት፣ ይስሙኝ ልንገራችሁ አይነት አቀራረብን ማስወገድ፣ የአድማጮችን ምላሽ መቀበል፣ መርጃ መሳርያ ካስፈለገ መጠቀም፣ ከአድማጭ የሚመጡ ጥያቄዎች በቅደም ተከተል በማስታወሻ በመያዝ ለተጠየቁት ጥያቄዎች ገለፃ መስጠት፣ ስሜትን የሚስቡ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም፣ የተለመደውን ርዕስ እንግዳ በሆነ ጭብጥ መግለፅ፣ ፈገግ የሚያሰኝ ቀልድን በመከከል ማቅረብ፣

የድምፅ ቃና፣ አወራረድ፣ ፍጥነት፣ ሃይል፣ መጠን እንዲሁም የአካል እንቅስቃሴ አድማጭን የሚማርክ እንዲሆን መጣር፣ ከፍርሃት ነፃ በመሆን ሀሳባችን ማቅረብ፣ ንግግሩ የሚያሳስብ፣ የሚያመራምርና የሚያወያይ እንዲሆን መጣር፣ ለቃላት ምርጫ ልዩ ትኩረት መስጠት፣ እኔ ብቻ ልደመጥ የሚል መንፈስ ማስወገድ፤ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።

2.5.3. የድህረ ንግግር ተግባራት

የድህረ ንግግር ተግባራት ተናጋሪው አድማጩን መልእክቱ ምን ያህል እንደተረዳው የሚገመግሙበት ተግባር ነው። የተወሰኑትን አድማጮች በዘፈቀደ በመምረጥ የንግግሩን ፍሬ ሃሳብ አስመለክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ከዚህም በተጨማሪ መጠይቅ አዘጋጅቶ አድማጮች እንዲሞሉ በማድረግ መልእክቱ በሚገባ መተላለፍና አለመተላለፉን ማረጋገጥ ይቻላል።

## 2.6. የንግግር ክሂል መመዘኛዎች

የንግግር ክሂል እንደማንኛውም ክሂል ሊመዘንና ሊለካ ይችላል፤ ከመለኪያ ነጥቦች መካከል የንግግሩ ሰዋስዋዊነት፣ የአንደበተ ርቱዕነቱ ደረጃ፣ የተፈለገው የንግግር አቀራረብ ሂደት መጠበቁ፣ ተገቢ ቃላትን የመጠቀሙ ችሎታና ተፈላጊውን መልእክት የማስተላለፍ ብቃቱ፣ ዋና ዋና የክሂል መመዘኛ ነጥቦች ናቸው (Brown & Yule, 1983)።

## 2.7. የንግግር አይነቶች

ንግግር ክሂል የራሱ የሆነ የአቀራረብ ሥርዓትን የሚከተል፣ እንደ መማሪያ አውድና ዓላማ ሊለዋወጥ የሚችል በውስጡ የተለያዩ የንግግር አይነቶችን አቅፎ የያዘ ክሂል ነው። በመሆኑም

ንግግር ተራክቧዊ፣መደበኛና ዓውድ ተኮር በመባል በሦስት ይከፈላል (Bagate, 2002 እና ፀጌ ፣1994)።

2.7.1. ተራክቧዊ ንግግር

በሰዎች መካከል ማህበራዊ መስተጋብር በመፈጠር የሚከናወን የዘወትር ንግግር ነው። የዚህ ዓይነቱ ንግግር የሰላምታ ልውውጥን፣ የእንግዳ አቀባበልና ሽኝትን፣ የምስጋና አቀባበልን፣ የንግግር አጀማመርና አጨራረስን፣ ወዘተ. ስርዓት ይመለከታል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በእነዚህ ክንውኖች ሲለማመዱ በቋንቋ መጠቀምን ብቻ ሳይሆን የቋንቋው ተናጋሪዎች ባህልና ልምድም ተግባራዊ ያደርጋል።

2.7.2. መደበኛ ንግግር

ከተራክቧዊ ንግግር በኋላ የሚቀርብና በመልእክት ላይ ትኩረት በማድረግ መደበኛ የንግግር ስርዓትን የሚከተል የንግግር ዓይነት ነው። በዚህ ወቅት የሀሳብ ፍሰትን፣ ተከታታይነትን፣ ቀጥተኛነትና እውነተኛነትን፣ ወዘተ. ጠብቆ መናገር ትኩረት ይደረግበታል።

2.7.3. አውድ ተኮር ንግግር

የተለያዩ የመነጋገሪያ አውዶችን በመፈጠር ተማሪዎቹ የተጋለጡበትን ዓውድ ወይም ሁኔታ ለመግለፅ በታላሚው ቋንቋ መናገርን የሚለማመዱበት የንግግር ዓይነት ነው።እነዚህን ተግባራት በበዓል አከባቢ፣ በቤተሰብ ጥየቃ፣ በአራስ፣ በሽተኛ ጥየቃ፣ በመዝናኛ ቦታ፣ በስፖርት ቦታ፣ በካፌ፣ በሆቴልና በቤተሰብ ምክክር፣ ወዘተ. ላይ የሚያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ።ለእነዚህ አውዶች የሚስማማ የቋንቋ አጠቃቀምና ቃላት መርጠው ሲገለገሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂላቸው ወደ ላቀ ደረጃ ያድጋል።

Brown (2007) የአነጋገር ስልቶችን አስመለክተው ርዕሰ ጉዳይ፣ አድማጭና ሁኔታ የሚለትን መደበኛ መስፈርቶችን በመጠቀም አምስት የንግግር ስልት ደረጃዎችን አስቀምጠዋል።

ምክክራዊ ስልት፡- በምልልስ የሚቀርብና በመጠኑም ቢሆን ጥንቃቄ ያልተለያቸው ቃላት የሚተገበሩበት ስሌት ነው። ለምሳሌ፡- ሀኪም ከበሽተኛው ጋርና በግብይት ወቅት በሻጭና በገዥ መካከል የሚደረጉ ንግግሮችን የሚመለከት ነው።

አንደበተ ርቱዕ ስልት፡- ይህ ስልት በህዝባዊ መድረኮች ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ለንግግሩ ትኩረት መስጠትን ማለትም የቃላት አመራረጥ ብቃትና የንግግሩ ድምፀት በሚገባ የተስተካከለ ንግግርን ይመለከታል።

ሆን ተብሎ ስልት፡- ይህ የንግግር ስልት ታዳሚውን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን፣ በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል በጣም ሰፊ እና ጠቃሚ የሆነ የሃሳብ ልውውጥ ይደረጋል። ለዚህ የንግግር ስልት ዋቢነት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚደረግ የመምህር ገለፃ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ጓዳዊ ስልት፡- ይህ ስልት ሙሉ በሙሉ የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት የሌለበት ሲሆን፣ ከቤተሰብ፣ ከፍቅረኛና ከጓደኛ ጋር የሚደረግ ንግግርን ይመለከታል። በአብዛኛው ጓዳዊ ስልት የተባለበት ውስጣችንን ገልፀን የምናወጣበት ንግግር በመሆኑ ነው።

ድንገቴያዊ ስልት፡- በጓደኛ እና በስራ ባልደረባ ወይም አንዳንድ ጊዜ በቤተሰብ መካከል የሚደረግ የንግግር አይነት ሲሆን ምንም አይነት ጥንቃቄ የማይታከልበት በነፃነት የሚነገር ነው።

ስለዚህ ክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት እነዚህን የአነጋገር ስልቶች እየተከተለ ተማሪዎችን ማስተማር በተማሪዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቅ ፋይዳ አለው።

## 2.8. የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ የትግበራ ዘዴዎች

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የንግግር ክሂል ተግባራት የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ተግባራቱ ተማሪዎች በጥንድ፣ በሦስትዮሽና በቡድን የሚያነጋግሩ፣ የተነሳሽነት ስሜት በመፈጠር ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል (Ur, 1996)። የንግግር ክሂል መማሪያ ተግባራት የራሳቸውን ባህሪያት አሉዋቸው። ከባህሪያቶቹ መካከል፡-

ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ሃሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ የሚያስችሉ፣ ፈጥኖ የመናገር ችሎታ ከፍ ለማድረግና ህፍረትን ለማስወገድ የሚረዳ፣ ሃሳብ የመግለፅን አቅም በማጎልበት ተጠየቃዊ በሆነ አካሄድ ነገሮችን መተንተን የሚያስችሉ መሆን አለባቸው (Ur, 1996)። እንደ Scrivener (1994:59) ገለፃ "በቋንቋ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ ንግግር በርካታ ዓላማዎች ቢኖሩትም ዋናው ዓላማ ለንግግር ትምህርት ዕድል ለመስጠት ነው። በልምምድ ወቅት ትኩረት የሚሰጠውም ከትክክለኛነት ይልቅ የቋንቋ ፍሰትን ለማሻሻል ነው" ይላሉ። ስለዚህ ተማሪዎች ለሚገኙበት ደረጃ ክፍል የሚመጥኑ የመለማመጃ ክንውኖች መምህራን በጥንቃቄ መምረጥ ይገባቸዋል። የንግግር ክሂልን ለማስተማር ክፍል ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ከስር ቀርበዋል።

ሥዕሎችን በንግግር መግለፅ፡- የመናገር ክሂልን በውይይት ለማስተማር በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ውጤታማ የሆነው ስእላዊ መግለጫ ነው። በዚህ ስልት ለማስተማር በቅድሚያ ተማሪዎችን በቡድን መከፋፈል ያስፈልጋል። በጥንድና በቡድን ተመድበው ለተቀመጡት ተማሪዎች የተለያዩ ስዕሎችን በማደልና በተወሰኑ ደቂቃዎች የስዕሎችን ይዘት የሚገልፁ ቃሎችን ወይም አረፍተ ነገሮችን እንዲመዘግቡ፣ የተመደበው ጊዜም እንዳለቀ ለጠቅላላው ተማሪ እንዲያቀርቡ በማድረግ የሚከናወን ነው (ማረው፣ 1998) ።

ልዩነትን በንግግር መግለፅ፡- ይህ የመማሪያ ስልት ተማሪዎችን በጥንድ በመመደብና የተለያዩ ነገሮችን በመስጠት በየግላቸው ካጠኑ በኃላ የአንዱ ከሌላው የሚለይባቸውን ባህሪያት በመናገር የሚለማመደበት ስልት ነው። በጋራ ሆነው በያዙዋቸው ነገሮች ልዩነት ላይ ሲወያዩ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችና የሚሰጧቸው መልሶች ሃሳባቸውን ነፃ ሆነው እንዲገልፁ ያደርጓቸዋል፤ ለተማሪዎች የመናገር ክሂላቸውንም ያዳብርላቸዋል።

የመረጃ ክፍተትን መሙላት (**Information Gap Filing**)፡- በጥንድ ወይም በቡድን የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ የመልመጃዎቹ ዓላማ መረጃ የሌላቸው ተማሪዎች መረጃ ካላቸው ጋር እንዲነጋገሩ ለማድረግ ነው (Bagate,1987)። ለመረጃ ክፍተት መሙላት አመቺ የሆኑ የንግግር ተግባራት አቅጣጫ ማሳየት፣ ቀጠሮ መያዝ፣ ንፅፅር እና ትረካ የመሳሰለት ናቸው (Bagate, 1987 & Harmer, 2007)።

በተመሳሳይነት መናገር፡- ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት በቡድንና በጥንድ ተመድበው በጋራ የያዙዋቸውን ነገሮች የጋራ የሆኑ ተፈጥሯዊ ባህሪያት በንግግር በመግለፅ ክሂሉን የሚለማመደበት ስልት ነው።በሂደቱም በቅድሚያ በየቡድናቸው እንዲቀመጡና የሚጋሯቸውን ነገሮችና ባህሪያት እንዲዘረዝሩ ግልፅ መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት ከፍተኛ ድረጃ የሚጫወተው መምህሩን ነው።

ችግርን የመፍታት ተግባራት (**problem solving tasks**)፡- ይህ የንግግር ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው ተነጋግረው ለአንድ ችግር መፍትሔ የሚፈለግበት ነው (Brown,1980)። ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር ሂደት በኃላፊነት ላይ ያለውን ሰው በመወከል ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ የምክር አገልግሎትን ለመስጠት፣ውሳኔ ለመስጠት ወዘተ በታላሚው ቋንቋ የሚጠቀሙበትን ንግግርን የሚለማመደበት ክንውን ነው። የዚህ ዓይነቱ የመለማመጃ ክንውን ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ፣ ዕድሜ እና የእውቀት ዳራ ተገናዝቦ የሚቀርብ ነው። ልምምድ የመናገር ችሎታቸውን ከማዳበር በተጨማሪ ማህበራዊ ችግሮችን ከራሳቸው ጉዳይ ጋራ አያይዘው መፍትሔ የመሻት ልምድን ያዳብርላቸዋል።

ሚና ጨዋታ (**Role play**) ሚና ጨዋታ ተማሪዎች በራሳቸው ገጠመኝ ሆነ በሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዘው የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ለክርክርና ለውይይት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። በተጨባጨ ዓለም ያለ ድርጊቶችን ክፍል ውስጥ በማቅረብ ንግግርን ማስተማሪያ መንገድ ነው።ለምሳሌ ተማሪዎችን ሻጭና ሸማች በመሆን መናገርን የሚለማመደበት የገሀዱን ዓለም ዕውነታ በማስመሰል በመማሪያ ክፍል ውስጥ አውድ መፈጠር ይቻላል።

ድርጊታዊ እንቅስቃሴ (**Mime**)፦ ይህ ሁኔታ ቃላዊ ንግግር በሌለበት ሁኔታ በድርጊት የታጀበ በመሆኑ አንድ ተማሪ የድርጊት እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች ምን ማለቱ እንደሆነ ገምተው እንዲናገሩ የሚያበረታታ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ድርጊቱን በማየት በንግግር ሀሳባቸውን ለመግለፅ ያስችላቸዋል።

ታሪክን መናገር (**story Teling**) ፡- በዚህ ስልት የንግግር ልምምድ ለማድረግ የተለያዩ ነገሮችን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው

እንዲናገሩ ማድረግ፣ የየራሳቸው ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ ማበረታታትና ስላአዩኣቸው ወይም ስለአከናወኗቸው ነገሮች እንዲናገሩ ዕድል በመስጠት ክፍል ውስጥ ንግግር ማለማመድ ይቻላል።

ሀሳብን ማመንጨት(**Brainstorming**)፡- ተማሪዎች በተወሰነ ርዕስ ላይ ተመርኩዘው ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት ብዙ ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ የሚረዳቸው በመሆኑ በንግግር ክንውን ወቅት ተማሪዎች በግላቸው፣ በጥንድ እንዲሁም በቡድን በመሆን ሀሳብ እንዲያፈልቁ ማድረግ ይቻላል (Staab,1992)። ተማሪዎች የተለያዩ ክንውኖችን በሚተገብሩበት ጊዜ የሚከተለትን ነጥቦች ማጤን ይኖርባቸዋል። እነሱም፣ ርዕሱን በወረቀት ጫፍ ላይ መፃፍ፣ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ በአእምሯቸው የመጠላቸውን ነገር ሁሉ መናገር፣ ለሰዋስው አወቃቀሩ ሳይጨነቁ የተባለውን ነገር በአጭር ቃል ወይም ሀረግ መጻፍ፣ ሁሉም የቡድኑ አባላት አስተያየት በመስጠት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ፣ ወዘተ… የመሳሰሉት ናቸው።

ችግሮችን አፍልቆ መፍትሔ መሻት፡- ይህ ፅንሰ ሀሳብ ውሳኔ ሰጭነት ተግባርን የሚገልፅ ሲሆን ተማሪዎች ራሳቸው ማህበራዊ ሚና እንዳላቸው በማሰብ የሚከናወን ተግባር ነው። ተማሪዎች አንድን ሚና ተክተው የሚጫወቱት ተግባር ሳይሆን ችግሮችን በሀሳባቸው አፍልቀው የችግሮቹን አስገዳጅ ሁኔታዎች በቡድን የሚመረምሩበት ነው። አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ የኮሚቴ ስብሰባ፣ በአንድ ችግር ዙሪያ ህዝባዊ ውይይት ማካሄድ ለዚህ ተግባር ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። በተግባሩ የሚነሱ ችግሮች ከተማሪዎች ዕድሜ ፣ ፍላጎትና ችሎታ ወዘተ… ጋር ተገቢነት ያላቸው ከሆኑ ተማሪዎችን የማሳተፍ ኃይላቸው ከፍተኛ ነው (Bagate,1987)።

ድራማዊ ተግባር፡- ድራማዊ ተግባራት ተማሪዎች የተለያዩ የፈጠራ ዐውድችን ተጠቅመው ተፈጥሯዊ ችሎታቸውን ለማሳየት ለመኮረጅ ፣ራሳቸውን ለመግለፅ ፣በምልልስ ወይም በጭውውት መልክ ለማቅረብ ወዘተ.ዕድል የሚያገኙበት ነው (Atkins & Nuru, 1995; Mlay&Duff, 1978)። በመሆኑም ድራማዊ ተግባራት የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከማሳደግ አኳያ ያላቸው ጠቀሜታ ታውቆ በክፍል ውስጥ ማለማመድና መተግበር ንግግር ክሂልን በብቃት ለማስተማር ጠቃሚ ነው። መምህራን የንግግር ክሂልን ክፍል ውስጥ ሲተገብሩ መከተል ያለባቸው የንግግር ክሂል መማሪያ ተግባራት በሦስት ይከፍለዋቸዋል (Brown and Yule, 1983)።

(1ኛ) ቋሚ ግንኙነት ያላቸው ነገሮች **(static relationships**) ፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የሚካተቱ ነጥቦች አንድን ነገር ወይም ፎቶ ግራፍ መግለፅ፣ የተለያዩ ነገሮች እንዴት እንደሚቀናጁ መመሪያ መስጠት ወይም መግለፅ፣ አንድን ሰው አንድን ነገር እንዴት እንደሚያከናውን መመሪያ መስጠት፣ ወዘተ… ናቸው።

(2ኛ) ተለዋዋጭ ግንኙነት ያላቸው **(Dynamic relation ships**) ፡- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የሚካተቱ ነጥቦች ታሪክ መናገር፣ የአይን እማኝ ወይም ምስክርነት መስጠት፣ ወዘተ.ተጠቃሽ ናቸው፡፡

(3ኛ) ረቂቅ ግንኙነት ያላቸው **(Abstract relationships**)፡- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የሚካተቱ ነጥቦች በአንድ ነገር ላይ አመለካከትን ወይም ሀሳብን መግለፅ፣ የአንድ ነገር ድርጊት ግልፅ ማድረግ፣ ወዘተ.የመሳሰለት ናቸው። ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ንድፈ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ተግባራት በአግባቡ ክፍል ውስጥ መተግበር የተማሪዎች የመናገር ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ከአከባቢያቸው ካለው ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ጋር በማያያዝ ንግግርን በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል።

## 2.9. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ

የንግግር ክሂል ትምህርት ክፍል ውስጥ ለማስተማር እንደ ዝግጅቱ ሁሉ አቀራረቡም ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው (Celce-murcia, 2001) ። ስለዚህ ንግግርን የማስተማር ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተለውን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ክፍል ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ Byrne (1992) ያስረዳሉ።

### 2.9.1. ትውውቅ

በዚህ ደረጃ የመምህሩ ተግባር እንደ መረጃ አቀባይ (Informant) መሆኑ ነው። መምህሩ የተለያዩ አዳዲስ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀምና በተቻለ መጠን በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበውን ተግባር ግልፅና በማይረሳ መልኩ ማቅረብ አለበት። በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርቱ በምልልስ መልክ ወይም በንባብ መልክ የሚቀርበው ጉዳይ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያሳድግ የሚችል አግባብነት ያለው ፣ አጭር መልስ የሚፈልግ ተስማሚ የሆነ ቋንቋ፣ የእውኑ

ዓለም ሰዎች ሊያደርጉት የሚችሉና ከክፍል ደረጃው ጋር ተመጣጣኝነት ያለው የንግግር ተግባር ባህርያትን ያሟላ መሆን ይገባዋል።

2.9.2. ልምምድ

የንግግር ክሂል ትምህርት ክፍል ውስጥ ለማስተማር እንደ ዝግጅቱ ሁሉ አቀራረቡም ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው (Celce-murcia, 2001)። ስለዚህ ንግግርን የማስተማር ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተለውን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ክፍል ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ Byrne (1992) ያስረዳሉ።

በልምምድ ወቅት አብዛኛውን ተግባር የሚያከናውኑት ተማሪዎች ናቸው። አስቀድሞ በቀረበው የትምህርት ዐውድ መሰረት በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ለማዳበር የሚለማመደበት ደረጃ ነው (Byrne, 1987)። ተማሪዎች ገምተው እንዲናገሩ፣ በቃል ማብራሪያ እንዲያቀርቡ፣ ሌሎችን መስለው እንዲናገሩ የሚያስችሉ ማለማመጃዎች ክፍል ውስጥ በማቅረብ ተግባራዊ ልምምድ እንዲያካህዱ የሚደረግበት ነው። ለምሳሌ ክፍት ቦታውን እንዲሞሉና ጥያቄዎችን በማምጣት እርስ በራሳቸው ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣ አንድ ስዕል በመስጠት በስዕሉ ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ነገሮችን እንዲገምቱ፣ ጅምር አረፍተ ነገሮችን እየጨረሱ እንዲናገሩ፣ ወዘተ. በማድረግ ተማሪዎች ማለማመድ የሚቻልበት የአቀራረብ ደረጃ ነው።

2.9.3. አፍልቆት

በዚህ ደረጃ ማንኛውም የመናገር ዕድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙበት እና በነፃነት እንዲገልፁ ማድረግ ነው። በአፍልቆት ደረጃው ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላልና በነፃነት የሚግባቡበት ዐውድን መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

## 2.10. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች የተከለሱበት ነው። ከእነዚህም ጥናቶች እጅጉ (2003 ዓ.ም) በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ ላይ የተደረገው ጥናት፤ አያልሰው (2003 ዓ.ም) ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ትምህርት መጻህፍት ውስጥ

በሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና ግምገማ፤ አዘነ (2003 ዓ.ም) በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ እና ሰለሞን (2010 ዓ.ም) በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ተቃኝተዋል።

ሰለሞን (2010 ዓ.ም) የጥናታቸው አላማ የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው በተመረጡ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ ተሳታፊዎች የእነዚህ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። የጥናቱም መረጃዎች ከተሳታፊዎች በክፍል ምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅ እና በቃለመጠይቅ ተሰብስበው ተተንትነዋል። የጥናቱም ውጤት በተወሰኑ መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸውን፣ በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር ሀሳባቸውን በነፃ የሚገልጹ በትን ሁኔታ አለማመቻቸታውን፣ የመናገር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ በተጨማሪም ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ የዕለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ርእሰ ጉዳይ ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል አለመስጠቱ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት የተሻለ ሙከራ አለመደረጉ አመላክቷል። የሰለሞን ( 2010 ዓ፣ም) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመናገር ክሂል ማተኮሩ፣ የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች የጽሀፍ መጠይቅ እና የክፍል ምልከታ ተግባራዊ ማድረጉ እና ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ እና መጠናዊ ምርምር ዘዴን ሲሆን አቀራረቡም ገላጻዊ መሆኑ ናቸው። የሚለየው ጥናቱ ያተኮረባቸው የክፍል ደረጃዎች (የሰለሞን በአስረኛ ክፍል መጠናቱና ይህ ጥናት በስምንተኛ ክፍል ማተኮሩ) እና ተሳታፊ መምህራንም የእነዚያ ከፍል ደረጃ መሆናቸው ነው።

አያልሰው( 2003 ዓ.ም) ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ትምህርት መጻህፍት ውስጥ በሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና ግምገማ ላይ ያተኮረ ጥናት ነው። ጥናቱም በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ ያለመሆኑ፣ የንግግር ክሂል ለማስተማር

የተለያዩ ዘዴዎችን (ስዕሎችን፣ ቃለ መጠይቆችን፣ ክርክሮችን፣ ጭውውቶችን ወዘተ) አለመጠቀም እና የመናገር ክሂል መልመጃዎችን አዘገጃጀት መርሆዎችን ያልተከተሉ መሆናቸውን አመላክተዋል። የአያልሰው( 2003 ዓ.ም) ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ በሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ ላይ ማተኮሩና የተለያዩ የሁለተኛ ደረጃ ክፍል ደረጃዎችን መመልከቱ ነው። ምክንያቱም ይህ ጥናት በስምንተኛ ክፍል ላይ ያተኮረ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፈትሹዋል ።

የአዘነ (2003 ዓ.ም) ጥናት በተመረጡ ሶስት የመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር ተገቢነት የፈተሸ ነው። ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ዘዴና ገላጭ ምርምር ንድፍ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን፣ መረጃዎች በክፍል ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበው ተተንትነዋል። የጥናቱ ውጤትም መምህራን የመናገር ክሂልን በተግባር ከማስተማር ይልቅ በገለፃና በማብራሪያ ላይ ተመስርተው ማስተማር፣ መምህራን የትምህርቱን አላማ በግልፅ ለተማሪዎች አለማስተዋወቅ፣ ትምህርቱን ከመጀመራቸው በፊት የሚያዝናኑ ነገሮችን አለመጠቀማቸው፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳተፎ እድል አለመስጠት፣ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች አተገባበርን በተመለከተ የስራ ላይ ስልጠና ባለማግኘታቸው ተማሪዎች መናገርን በተግባር እንዲማሩ የማድረግ ሚናቸውን በአግባቡ እየተወጡ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፤ በተጨማሪም በማስተማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ለማስተማሪያነት የቀረቡት የመናገር ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች ጥቂት መሆናቸውና ከነዚህም መካከል መምህራን አዘውተረው የሚጠቀሙት የተወሰኑትን ብቻ ማለትም ክርክርን፣ የቡድን ውይይትና አንድ አንድ ጊዜ ጭውውትን እንደሆነና ለአንድ ክፍለ ጊዜ የተመደበው ሰዓት በቂ አለመሆኑ ን ለመገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ የመናገር ክሂል ትምህርት መልመጃዎች መተግበር ባለባቸው አግባብ እየተተገበሩ አለመሆኑን አረጋግጠዋል። የአዘነ (2003 ዓ.ም) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለወ መረጃው በክፍል ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብሰቦ መተንተኑ ነው። የሚለየውየአዘነ ጥናት የክፍል ውስጥ የመልመጃዎች አተገባበር ላይ ማተኮሩ እና የክፍል ደረጃው ሰባትኛ መሆኑ ናቸው። ምክንያቱም ይህ ጥናት በስምንተኛ ክፍል ላይ ያተኮረ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፈትሹዋል።

እጅጉ (2003 ዓ.ም) በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ላይ የተደረገ ግምገማዊ ጥናት ነው። በመማሪያ ክፍል ውስጥ የነበረውን አጠቃላይ አተገባበር ገምግመው ይፋ ያደረጉት ውጤት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ተግባራዊ መደረግ የነበረባቸው ብልሃቶች አለመከናወናቸውን ገምግሟል። በተለይ በቡድን ውይይት፣ የግል፣ የጥንድ ወዘተ... ማቅረቢያ ዘዴዎችን መምህራን መተግበር አለመቻላቸውን፣ የተማሪዎች ተራክቦ እኩል እንዳልሆነና የተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት አለመተኮሩ እና የትግበራ ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች ያሳተፈ አለመሆኑን አረጋግጠዋል። የእጅጉ (2003 ዓ.ም) ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው የመናገር ክሂል አቀራረብ ላይ ያተኮረ ግምገማዊ ጥናት ማካሄዱና በሰባተኛ ክፍል ላይ ማተኮሩ ነው። ምክንያቱም ይህ ጥናት በስምንተኛ ክፍል ላይ ያተኮረ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፈትሹዋል።

ስለሆነም ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች ከቦታ በተጨማሪ በክፍል ደረጃ ይለያል። የተጠኝዎች መለያየት ለጥናቱ ዉጤት መለያየት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከክፍል ደረጃ በተጨማሪ ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናነቶች የሚለየዉ በዘመን ነዉ። የመምህራን አሰለጣጠን ከዘመኑ ዕድገት ጋር ለዉጥ ስለሚያሳይና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ማሻሻያ ስለሚደረግባቸዉ በጥናቱ ዉጤት ላይ ለዉጥ ያስከትላል። በንግግር ክሂል አቀራረብ የመምህር-ተማሪ ተራክቦን ትኩረት ሰጥቶ ማየቱ ሌላዉ ልዩነት ነዉ።

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴዎች

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ዓይነትና አደረጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰቡ ሂደትና የጥናቱ አጠናን ሥልት በዝርዝር ቀርበዋል። ጥናቱም ዓይነታዊ እና አሃዛዊ በቅይጥ የምርምር ዘዴን የተከተለ (Mixed approach) ነዉ። ይህም ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በሁለቱ መንዶች የተሰበሰቡ መረጃዎች እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን እንዲደጋገፉ ለማድረግ ሲባል ነው። በDcmyei (2007:32)እንደሚሉት የዓይነታዊ ምርምር መረጃዎች አቀራረቡም ገለፃዊ ዘዴን (Descriptive Method) ተግባራዊ አድርጓል።

## 3.2. የጥናቱ ናሙናዎች አመራረጥ

ጥናቱ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያተኩር ነው። በወላይታ ሶዶ ከተማ የሚገኙ ሁለም ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ማካተት ከሰው ኃይል፣ ከገንዘብና ከጊዜ እጥረት አኳያ የሚቻል አልሆነም። ስለሆነም በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግል የትምህርት ቤት፣ የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና መወሰን የግድ ነበር። ወካይ ናሙናዎቹን በመምረጥም የተለያዩ ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል። በከተማ አስተዳደሩ ካሉ 8 አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በዕጣ ንሞና 3 ወካይ ት/ቤቶች ተመርጠዋል። በት/ቤቶቹ ከሚማሩት 620 ተማሪዎች ዉስጥ 20 በመቶ (20%) ማለትም 124 ተማሪዎች ዕጣ በማዉጣት ዘዴ ተመርጠዋል። በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ በሁሉም ትምህርት ቤቶች በየክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን በአጠቃላይ ንሞና ዘዴ (Comprehensive Sampling) በጥናቱ ተካተዋል።

ዘዴዎቹና አጠቃሊይ የአመራረጥ ሂደቱ እንደሚከተው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አንድ፤ የተመረጡ የትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎችና የመምህራን መረጃ

| ተራ ቁጥር | የትምህርት ቱ ስም | የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች | | የአማርኛ ቋንቋ መምህራን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ ብዛት | ናሙና ብዛት | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ሊጋባ በየነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 194 | 39 | 2 | 1 | 3 |
| 2 | ትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 147 | 30 | 1 | 1 | 2 |
| 3 | አብዮት ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 279 | 55 | 4 | 1 | 5 |
| ጠቅላላ ድምር | | 620 | 124 | 7 | 3 | 10 |

በሰንጠረዥ አንድ ከቀረበው መረጃ የምንረዳው በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድ 256 እና ሴት 364 በድምሩ 620 ናቸው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን 7 ወንድ እና 3 ሴት በድምሩ አስር ናቸው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ከተመረጡ ናሙናዎች መረጃዎች ያስፈልጋሉ። ስለሆነም ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ምልከታ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የመረጃዎች አሰባሰብ ከመከናወኑ በፊት አስተማማኝ እንዲሆኑ በጥናቱ አማካሪና በደረጃው በሚያስተምሩ የሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው መምህራን አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል። የማሻሻያ ሃሳቦችም ታክለው ተተግብሯል።

### 3.3.1. የጽሁፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በተማሪዎችና መምህራን ተግባራዊ የመደረጉ አላማ በክፍል ምልከታ ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ለማመሳከር ነው። የጥያቄዎች አላማ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች አንድ ሲሆን፣ ትኩረት በንግግር ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ከመምህራን አኳያ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። የፅሁፍ መጠይቁ የምልከታ መከታተያ ቅፅ ዉስጥ የተካተቱትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ነዉ። የጽሁፍ መጠይቁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ሙከራ ተደርጓል። በሙከራዉም የተወሰኑ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። የፅሁፍ መጠይቁ ለመምህራንና ተማሪዎችን በቂ ጊዜ ወስደው እንዲሞሉ ተደርጓል። በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች መጠይቁን በሚሞሉበት ወቅት አጥኚው በስፍራው በመገኘት ማብራሪያዎችን ሰጥቷል። ለተማሪዎች 14 እና ለመምህራን 18 ዝግ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ የተሰራጩ መጠይቆች በተገቢው መንገድ ተሰብስበዋል (አባሪ 1፣ 2፣ 5 እና 6 ን ይመልከቱ)።

### 3.3.2. የክፍል ምልከታ

በዚህ ጥናት ተግባረዊ የተደረገው ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል ለምልከታ በተዘጋጀ ፎርማት መሰረት ተከታታይ ምልከታዎች ተደርገዋል፡፡ የክፍል ምልከታዉ ሁሉም ጥያቄዎች በዝግ ጥቄዎች ቀርበዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የተደራጀ ምልከታ (Structured observation) በክፍል ዉስጥ በሚከናወኑ የተወሰኑ የትኩረት አቅጣጫዎችና ጠጨባጭ በሆኑ የምልከታ ነጥቦች ላይ ለማተኮር ነዉ (Domyei, 2007:163)፡፡ የሚሰበሰበዉን መረጃ አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ በትግል ፍሬ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በሙከራዉም የተወሰኑ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የምልከታው ሂደት በጥንቃቄ የተከናወነ ሲሆን ከመጋቢት 5 እስከ ግንቦት 5 ያለውን ጊዜ ሸፍኗል፡፡ የምልከታው ቅጽና የተጠቃለለው ውጤት አባሪ ተደርጓል (አባሪ 3 እና 4 ን ይመልከቱ)፡፡

## 3.4. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስና የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ በጽሁፍ መጠይቅ እና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በመልሶቹ ላይ በማጣራት፣ ኮድ የማድረግ ሂደት ከተከናወነ በኃላ የመለየትና የማደራጀት ስራ ተከናዉኗል፡፡ በኋላ ተተንትነዋል፡፡ የትንተናው ሂደት መጠይቆችን በይዘታቸው እና በምድባቸው በመከፋፈል በሰንጠረዥ ቀርበው ውጤቱ መቁጥርና በመቶኛ ተገልጹዋል፡፡ ይህም በቁጥርና መቶኛ የቀረበው ውጤት በገላጻ ስልት ተብራርቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ውጤት ትንተናና የዉጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶዶ ከተማ በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፈተሽ ነዉ። ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ ምን ይመስላል? ፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርትን አተገባበር ወቅት የልምምድ ሂደቱ ምን ይመስላል? እና በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ? የሚሉ ናቸው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ጥያቄዎችን ለመመለስ መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ምልከታ መረጃዎች ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ በገለጻ ስልት ተብራርተዋል። በሚከተለው መልኩ ይቀርባል።

## 4.1. ከጽሁፍ መጠይቅ እና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.1.1. የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ የመረጃዎች የትንተና ውጤት

በዚህ ጥናት ምላሽ ከሚሰጣቸው ጥያቄዎች የመጀመሪያው የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚል ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከክፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎችና ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል።

የሁለቱም መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች የትኩረት ነጥቦች በመማር ማስተማር ሂደት በንግግር ትምህርት አቀራረብና አተባበር በክፍል ውስጥ የሚከናውኑ ትግባራት ለትምህርትነት የቀረበውን ይዘት አላማ መግለጽ፣ የትግበራ ሂደቱና አቀራረቡ የተማሪዎችን እድሜና ደረጃ ያገናዘበ እንዲሆን በተማሪዎች የመማሪ መጽሐፍና መርሃ ትምህርቱ ላይ እንዲመሰረት ማድረግ፣ ተማሪዎች በንግግር ወቅት ፈጠራን መለማመድ የሚያስችሉ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ማቅረብ፣ በቂ የልምምድ ተግባራትን ማቅረብ ተማሪዎች እንዲነቃቁ ሊያተኩር ይገባል። ከእነዚህ ነጥቦች አኳያ

በተመረጡ ሶስቱ ትምህርት ቤቶች የክፍል ውስጥ ምልከታ ተደርጓል። የትንተናው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 4.1. የመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ በተመለከተ የክፍል ምልከታ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ትግበራ ዘዴ | የምላሽ አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | በመቶኛ | አይ | በመቶኛ |
| 1 | የመናገር ትምህርት ለማስተማር ስለቀረበው ይዘት ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | 6 | 60% | 4 | 40% |
| 2 | በክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርቱ አቀራረብ መርሃ ትምህርቱንና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | 10 | 100% | - | - |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የተማዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | - | - | 10 | 100% |
| 4 | የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 5 | የመናገር ትምህርቱን ለማስተማርና ለመማር በቂ የልምምድ ተግባራት ቀርበው እንዲለማመዱ እየተደረገ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | 3 | 30% | 7 | 70% |
| 6 | የመናገር ትምህርት ለማስተማርና ለመማር የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችና ተግባራት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | 9 | 90% | 1 | 10% |

በሰንጠረዥ 4.1. የቀረበው መረጃ እንዳመለከተው የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ በተለያዩ ቀናት በተከታተይ የክፍል ምልከታ ተከናውኗል። በእነዚህ ቀናት በነበረው የክፍል ምልከታ ወቅት ለተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርት በሚቀርብበት ጊዜ የትምህርቱን ይዘት ዝርዝር አላማ በመግለጽ እና በማስተዋወቅ የጀመሩ መምህራን ስድስት (60%) ሲሆኑ፣ ሌሎች አራቱ (40%) አላማ ሳይገልጹ ጀምረዋል።እንደ ቋንቋ ምሁራን እምነት አንድ መምህር አንድን የትምህርት ይዘት ለማስተማር ክፍል ሲገባ ከሰላምታ ቀጥሎ የተለያዩ ጥያቄዎች በማንሳት የቀደመውን ትምህርት ካስታወሰ በኋላ የእለቱን የትምህርት ይዘት አላማ በዝርዝር መግለጽ አለበት። ይህም ተማሪዎች የመናገር ክሂል ሲማሩ ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ስለሚጠቁም ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ለትምህርትነት የተመረጠው አወድ ከተለያዩ ማህበራዊ

ጉዳዮች፣ ባህል፣ ወግ፣...ወዘተ. ሊተሳሰር ስለሚችል ከመናገር ክሂል ለማያያዝ አላማው ሊታወቅና ሊገለጽ ይገባል። ነገር ግን ከአስሩ መምህራን አራቱ ለተማሪዎች የትምህርት ይዘቱን አላማ ሳይገልጹ ቀጥታ ወደ ማስተማር ሂደተ ገብተዋል። ይህም የትምህርት ይዘት አላማ ከትምህርቱ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን ውጤት እና ለውጥ የሚጠቁም ዋናው ቁምነገር መሆኑን ከመዘንጋት ወይም ትኩረት ካለመስጠታቸው ጋር የሚያያዝ ነው። በአጠቃላይ ዓላማ ሊደረስበት የተወሰነ ውጤት ሲሆን፣ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ይዘት የሚሰጣቸውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚያከናውኑት፣ የሚደርሱበት እና የሚያውቁት ተግባር ነው። ይህን ሃሳብ በማጠናከር ታደሰ (2004 ዓ.ም) እንደገለጹት፣ የትምህርት ይዘቶች አላማቸው ሌሎች ተጠቃሚዎች በቀላሉ በሚገነዘቡበት መልኩ ሊገለጽ ይገባል።

በዚህ ሰንጠረዥ ከተገለጹ የመረጃ ትንተናዎች የተካተተው ለተማሪዎች የቀረበው የንግግር ትምህርት በመማሪያ መጽሐፉና በመርሃ ትምህርት ላይ ተመስርቶ መቅረቡን ማረጋገጥ ነበር። አስሩም (100%) መምህራን የትግበራ ሂደታቸው በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተመሰረተ ነው። የትምህርት ይዘቱ ወይም ለትግበራ የቀረበው ርዕስ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተመሰረተ ነበር። እንደ ታሰደ (2004 ዓ.ም) ገለጻ፣ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ከትምህርት ዓላማው ጋር ካላቸው ተጣጥሞሽ፣ ተማሪው ቋንቋውን በሚገባ እንዲጠቀም ከማስቻላቸው፣ የተማሪዎችን ፍላጐትና ስሜት የብስለት ደረጃ እድሜና ባህል ከማገናዘባቸው አኳያ፣ በቋንቋው፣ በስነዘዴውና በተማሪው መካከል ግንኙነት ከመፍጠራቸው አንጻር ሊመረጡ ይገባል።" ምርጫው ብቻውን በቂ ስላልሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርት ይዘቶች አማካይነት ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ጥናት የክፍል ምልከታ መረጃ ትንተናው የመናገር ክሂል የትምህርት ይዘቱ አቀራረብ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ መመስረቱን አመልክቷል።

ፈጠራን የሚያበረታቱ መምህራን ጠንካራ እውቀት ያላቸው ናቸው። እነዚህ መምህራን ለተማሪዎች የሚያቀርቡትን የትምህርት ይዘት ሲያዘጋጁ ፈጠራ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይጥራሉ። ይህ ለማረታታት የሚቀርቡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሊመረጡ ይገባል። ምክንያቱም የሚተነተኑ፣ የሚገመገሙ እና የሚመሩ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው። በእንዲህ መልኩ የሚዘጋጁ የንግግር ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የተለያዩ ችሎታዎችን እንዲያዳብሩና በጥልቀት የማሰብ

ደረጃቸውን ከፍ ያደርጋል። እንዲሁም በመማር ሂደታቸው ተነሳሽ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል (Richards, 2013)።

በዚህ በክፍል ምለከታ ወቅት የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ሰላቅረቡ ተፈትሾ አስሩም መምህራን (100%) የተማሪዎችን ፈጠራን የሚያበረታታ እና ማስተማሪያ መሳሪያ ያልቀረበበት ነው። ይህም ትኩረት ያነሰው መሆኑን ያሳያል።ንግግር ስሜት ያፈለቀውን፣ ዓይን የተመለከተውን ወይም ከንባብና ከማዳመጥ የተቀሰመውን ግብዓት መነሻ በማድረግ ሀሳብን ሥርዓት ባለው መንገድ ለሌላ ወገን ለማስደመጥ መሞከር ነው (ታሰደ፣ 2004 ዓ.ም)። ይህን ለማሳካት በተገቢውን መንገድ የተማሪዎችን የመማር ደረጃ ያገናዘቡ የትምህርት ይዘቶች ተዘጋጅተው መቅረብ ቢችሉ። ከዚህ አኳያ በመምህራን የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ መሆኑን ለማረጋገጥ የክፍል ምልከታ ተደርጓል። በዚህ መሰረት አምስት ( 50%) መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ይዘት ያቀረቡ ሲሆን፣ ቀሪ አምስቱ (50%) ይህ ማድረግ ያልቻሉ ናቸው። በምልከታ ወቅት ከቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ለምሳሌ፣ በመምህሩ ተነሳሽነት የተማሪዎችን የሳይንስና የፈጠራ ክህሎታቸዉን የሚያዳብሩ እንዲሁም "የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀገራዊ ፋይዳውን በተመለከተ በምክንያት እያስደገፋችሁ ተወያዩ የሚል ነበር። ይህ ጽንሰ ሃሳብ ለብዙ ተማሪዎች እንግዳ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎች ግራ ሲጋቡ ታይተዋል። እንዲህ አይነቱን የትምህርት ይዘት ለማቅረብ ተማሪዎች ስለጉዳዩ ዳራዊ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፤ ካልሆነም በመነጋገሪያ ርዕሱ ላይ አንብበው መረጃዎችን አሳበስበው እንዲመጡ ማድረግ ይቻል ነበር። ውጤቱም የሚያመለክተው በተወሰኑ መምህራን በኩል የተዘጋጀው የንግግር ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘት በተማሪዎች ላይ እንዲመጣ የሚፈለገው ለውጥ ያልመጣ መሆኑን ያስረዳል።

ለተማሪዎች በትምህርትነት የሚቀርቡ ይዘቶች አላማቸው ሊሳካ የሚችለው በተለያዩ የልምምድ ተግባራት ሲታጀብ ነው። እነዚህም የልምምድ ተግባራት ተማሪዎችን ለመናገር የሚያነሳሱ እና እንዲለማመዱባቸው ሆነው መቅረብ አለባቸው። ተማሪዎችን እንዲናገሩ ማነሳሳት በመናገር ሂደት ጥሩ ተግባቦት እንዲያከናውኑ ያሰፈልጋቸዋል (Nerfi, 2013):: ከዚህ አንጻር መምህራን

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርቱን ለማስተማርና ለመማር በቂ የልምምድ ተግባራት ቀርበው እንዲለማመዱ እየተደረገ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር መከናወኑን ለማረጋገጥ ምልከታ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ሶስቱ (30%) መምህራን በቂ የልምምድ ተግባራትን አቅርበው ሲያስተምሩ፤ ሰባቱ (70%) መምህራን ደግሞ ውስን ተግባራት በማቅረብ ተለምዷዊ በሆነ መንገድ ተነጋገሩ፤ ስሩ፤ እያሉ ያዟቸው ነበር፡፡ በክፍል ምልክታው ወቅት ተማሪዎች ወደ ንግግር ተግባር ከመግባታቸው በፊት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ተማሪዎች ለንግግር እንዲዘጋጁና እንዲነቃቁ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ክፍተት ታይቷል፡፡ አብዛኛው መምህራን በዕለቱ የሚያስተምሩትን የንግግር ትምህርት ይዘት "ሰላም ለሰው ልጆች ባለው ጠቀሜታ ላይ ተወያዩ" የሚል ትዕዛዝ በመስጠት ወደ ማስተማር ሲሸጋገሩ ታይተዋል፡፡ የመናገር ክሂል በማስተማር ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ አለማድረግ የሚፈለገውን ያህል እንዲናገሩ እድል አይሰጣቸውም፡፡ እንዲሁም የልምምድ በተግራት ውስን መሆን ተማሪዎች ተሳትፏቸው እየቀነሰ ስለሚመጣ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን የመናገር ትምህርት ለማስተማርና ለመማር የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችና ተግባራት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ በግልፅ መሆናቸውን በተመለከተ በምልከታው ተዳሷል፡፡ ከመመሪያዎች ግልጽነት አኳያ ሲታይ ዘጠኝ (90%) መምህራን ባቀረቡት የልምምድ ተግባራት የትግበራ መመሪያዎች በግልጽ የቀረቡ ሲሆን፣ አንድ (10%) መምህር በግልጽ ሊያቀርብ አልቻለም፡፡ የምልክታውን ውጤት ለማመሳከር ለተማሪዎች ከተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እንሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 4.2.፡- የመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ

በተመለከተ የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | የተሰጠ ውጤት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፍጹም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አላማው ይገለጽልኛል። | 49 | 39.51% | 51 | 41.13% | 8 | 6.45% | 12 | 9.68% | 4 | 3.23% |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባር በክፍልውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ማነቃቂያ ይቀርብልኛል፡፡ | 34 | 27.41% | 42 | 33.87% | 18 | 14.52% | 21 | 16.94% | 9 | 7.26% |
| 3 | የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመሩ በፊት ግልፅ መመሪያ ይሰጠኛል። | 53 | 42.74% | 46 | 37.1% | 11 | 8.87% | 8 | 6.45% | 6 | 4.84% |
| 4 | የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የትምህርት ደረጃን ያገናዘበ ነበር። | 28 | 22.58% | 32 | 25.81% | 21 | 16.94% | 26 | 20.97% | 17 | 13.71% |

በሰንጠረዥ 4.2. የቀረበው መጠይቁ የመጀመሪያ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት የትምህርቱን ይዘት አላማ መግለጻቸውን የተመለከተ ነው። ለጥያቄው ከ124 ተማሪዎች በጣም አስማማለሁ 49(39.51%)፣ እስማማለሁ 51(41.13%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 8(6.45%)፣ አልስማማም 12(9.68%) እና በጭራሽ አልስማማም 4(3.23%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከተሰጡ ምላሾች በበጣም እሰማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 80.64 በመቶ ሆኗል። ይህም አብዛኛዎቹ መምህራን የትምህርቱን ይዘት አላማ ገልጸው ወደ ንግግር ተግባራት የሚሸጋገሩ መሆናቸውን አረገግጠዋል።

ሁለተኛው የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ማነቃቂያ የሚያቀርቡ ስለመሆናቸ ነው። ለጥያቄው ተማሪዎች በጣም አስማማለሁ 34 (27.41%)፣ እስማማለሁ 42 (33.87%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 18 (14.52%)፣ አልስማማም 21 (16.94%) እና በጭራሽ አልስማማም 9 (7.26%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የተማሪዎች ምላሽ የሚያመለክተው ከአስሩ መምህራን ስድስቱ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት ማነቃቂ የሚያቀርቡ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ለበጣም እሰማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 61.28 በመቶ ነው።

ሶስተኛው የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄ የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመሩ በፊት ስለተግባሩ አከዋወን በመምህራን ግልፅ መመሪያ መሰጠቱን የሚመለከት ነው። ለጥያቄው ምላሽ የሰጡ 124 ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በጣም አስማማለሁ 53(42.74%)፣ እስማማለሁ 46(37.1%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 11(8.87%)፣ አልስማም 8(6.45%)እና በጭራሽ አልስማም 6(4.84%) ሆኗል። ይህ የትንተና ውጤት ከምልከታው ውጤት ይቀራረባል። ምክንያቱም የጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ለበጣም እሰማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 79.84 በመቶ ነው። ይህ የመቶኛ ውጤት ከምልከታው ውጤት 90 በመቶ ጋር የተቀራረበ ነው። ስለሆነም ውጤቱ መምህራን ለንግግር ትምህርት ማስተማሪያነት ለሚቀርቡ ተግባራት ግልጽ መመሪያ የሚሰጡ መሆናችን ያመለክታል።

አራተኛው የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄ የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። በዚህ መሰረት ተማሪዎች በጣም አስማማለሁ 28 (22.58%)፣ እስማማለሁ 32 (25.81%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 21 (16.94%)፣ አልስማማም 26 (20.97%) እና በጭራሽ አልስማማም 17 (13.71%) ሆኗል፡
፡

የትንተናው ውጤት የትምህርት ይዘቱ የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ለመሆኑ የተማሪዎች ምላሽ ለበጣም እሰማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 48.39 በመቶ መሆኑ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች የግንዛቤ ደረጃ ጋር የማይመጣጠኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ይህም ከምልከታው ውጤት ጋር የተቀራረብ ነው።

ይህን ጥያቄ ለመመለስ በማመሳከሪያነት የቀረበው ለመምህራን የተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ ነው። ለመምህራን የተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄ ከክፍል ምልከታና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ጋር ይመሳሰላል። የጥናተናውም ውጤት እንደሚከተለው ይቀርባል።

ሰንጠረዥ 4.3.፡- የመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ በተመለከተ የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | **የተሰጡ ምላሾች** | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ሁልጊዜ** | | **አብዛኛውን ጊዜ** | | **አንዳንድ ጊዜ** | | **ጨርሶ** | |
| | | **በቁጥር** | **በመቶኛ** | **በቁጥር** | **በመቶኛ** | **በቁጥር** | **በመቶኛ** | **በቁጥር** | **በመቶኛ** |
| 1 | በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የመናገር ትምህርት ከማቅረቤ በፊት የትምህርቱን አላማው በግልፅ አብራራለሁ። | 4 | 40% | 5 | 50% | 1 | 10% | - | |
| 2 | ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሊያነቃቋቸው የሚችሉ ስራዎችን እሰራለሁ። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 3 | ስለ መናገር የክፍል ውስጥ አቀራረብ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት ስለአተገባበሩ ሂደቱ ግልጽ መመሪያ እሰጣለሁ። | 3 | 30% | 4 | 40% | 3 | 30% | - | |
| 4 | በትምህርቱ አቀራረብ የተማዎችን ፈጠራ በሚያበረታታ መልኩ የማስተማሪያ መሳሪያ አቀርባለሁ። | - | - | 1 | 10% | 1 | 10% | 8 | 80% |
| 5 | ተማሪዎቹ የሚቀረብላቸው የትምህርት ይዘት ከትምህርት ደረጃቸው ጋር የተመጣጠነ ነው። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |

በሰንጠረዥ 4.3. ለመምህራን የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት የትምህርቱን ይዘት አላማ መግለጻቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁልጊዜ 4 (40%)፣ አብዛኛውን ጊዜ 5 (50%) እና አንዳንድ ጊዜ 1(10%) እገልጻለሁ በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የመምህራን ምላሽ 90 በመቶ በክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት የትምህርቱን ይዘት አላማ የሚገልጹ መሆናችን ያመለክታል። ምክንያቱም 40% ሁልጊዜ እና 50% ባብዘኛው የሚገልጹ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ይህም ውጤት ከክፍል ምልከታው ጋር ስናነጻጽረው ልዩነት አለው። ምክንያቱም የምልከታው ውጤት 60 በመቶ የትምህርት ይዘቱን አላማ ገልጸው ወደ ተግባር መግባታቸውን አሳይቷል።

ለመምህራን ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሊያነቃቋቸው የሚችሉ ስራዎችን ስለመስራታቸው ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁልጊዜ 2(20%)፣ አብዛኛውን ጊዜ 3 (30%) እና አንዳንድ ጊዜ 5(50%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ውጤት ሁለት መምህራን ሁልጊዜ የሚያነቃቁ መሆናቸውን፣ ሶስቱ አብዛኛውን ጊዜ እና አምሰቱ አንዳንድ ጊዜ የሚያነቃቃ ስራ እንደሚሰሩ ያመለክታል። ይህ ውጤት ከክፍል ምልከታው አኳያ ሲታይ ሶስት መምህራን ተማሪዎችን አነቃቅተው ወደ ንግግር ተግባር መሸጋገራቸውን አሳይቷል። ውጤቱም የተቀራረበ ነው፤ ቢባልም ልዩነት አለው።

ሶስተኛው ለመምህራን የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄ ስለ መናገር የክፍል ውስጥ አቀራረብ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት ግልጽ መመሪያ መሰጠቱን የሚመለከት ሲሆን፣ ሁልጊዜ 3(20%)፣ አብዛኛውን ጊዜ 4 (40%) እና  አንዳንድ ጊዜ 3(30%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የመምህራን ምላሽ አብዛኛው መምህራን ግልጽ መመሪያ የሚሰጡ መሆናቸውንና የተወሰኑ መምህራን አንዳንዴ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን አመላክቷል። ይህም አንዳንድ መምህራን ተማሪዎችን ወደ መናገር ተግባር የሚመሩት የመናገርን ተግባር እንዴት ማከናወን ወይም ማቅረብ እንዳለባቸው መመሪያ ሳይሰጡ ያስጀምራሉ። ስለዚህ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና በማስተማሪያ መሳሪያ ታግዞ መቅረቡን በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦላዋል። የመምህራን ምላሽ አብዛኛውን ጊዜ 1(10%)፣ አንዳንድ ጊዜ 1(10%) እና ጨርሶ 8(80%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የትንተናው ውጤት ባንድ መምህር አብዛኛውን ጊዜ እና በሌላኛው አንድ መምህር አንዳንድ ጊዜ ፈጠራን የሚያበረታታ እና በማስተማሪያ መሳሪያ ታግዞ መቅረቡን ሲገልጹ፣ በስምንቱ (80%) መምህራን ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑ ተመልክቷል። ይህም የንግግር ትምህርት አቀራረብ ፈጠራ የማያበረታታ እና በማስተማሪያ መሳሪያ ታግዞ የማይቀርብ መሆኑና ከምልከታው ውጤትም ጋር የሚመሳሰል ስለሆን ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው።

ለመምህራን ለተማሪዎች የሚቀርበው የንግግር ትምህርት ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ስለመሆኑን ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁልጊዜ 2(20%)፣ አብዛኛውን ጊዜ 5(40%) እና አንዳንድ ጊዜ 3(30%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ውጤቱም 70 በመቶ መምህራን ሁልጊዜ እና

አብዛኛው ጊዜ የሚቀርበው የትምህርት ይዘት የተማዎችን የትምህርት ደረጃ ባገነዘበ መልኩ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡ በምልከታው ወቅት ከታየው ውጤት ተቀራራቢ ስለሆነ የትምህርት ይዘቶችን ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ የተገናዘበ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ክፍተቶች አሉ፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ በተመለከተ ከክፍል ምልከታ፣ ለተማሪዎችና ለመምህራን ከተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ውጤቱ ተቀምጧል፡፡ ይህም ውጤት መምህራን ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ተማሪዎችን ሊያነቃቋቸው የሚችሉ ስራዎችን ከመስራት፣ የተማሪዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና በማስተማሪያ መሳሪያ ታግዞ ከማቅረብ እና ትምህርት ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ችግር ያለ መሆኑን አመላክቷል፡፡

### 4.1.2. የተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የልምምድ ሂደት የመረጃዎች ትንተና

ይህ የሚመልሰው ሁለተኛው ጥያቄ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የልምምድ ሂደቱ ምን ይመስላል? የሚል ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ስር የተነሱ ትኩረት ነጥቦች የመናገር ትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚያደርጉት የልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ መታየቱን፣ የመናገር ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ስለመጠቀማቸው፣ የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ቀርቦ ስለመከናወኑ፣ የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን የማስተማር ስነዘዴ ስለመጠቀማቸው፣ ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት መናገር እንዲለማመዱ መበረታታቸውን፣ የመናገር ትምህርት ሲሰጥ የልምምድ ተግባራት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ስለመጠቀማቸው፣ በመናገር የልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ስለማበረታታቸው፣ በመናገር የልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ስለመሰጠቱ እና  በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ስለመደረጉ ናቸው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ መረጃዎች ከከፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎች እና

ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው የተተነተኑ ሲሆን እንደሚከተለው ይቀርባል፡
፡

ሰንጠረዥ 4.4. በመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራት ተሳትፎ እና ለማሳተፍ የተከናወኑ የክፍል ምልከታ መረጃዎች ትንተና

| **ተ.ቁ** | **የማስተማሪያ ትግበራ ዘዴ** | **የምላሽ አማራጮች** | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | **አዎ** | **በመቶኛ** | **አይ** | **በመቶኛ** |
| 7 | የመናገር ትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚያደርጉት የልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ ይታይ ነበር? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 8 | የመናገር ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 9 | የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ቀርቦ ተከናውኗል? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 10 | የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን የማስተማር ስነዘዴ ተጠቅመው ነበር? | 7 | 70% | 3 | 30% |
| 11 | ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት መናገር እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 12 | የመናገር ትምህርት ሲሰጥ የልምምድ ተግባራት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | 2 | 20% | 8 | 80% |
| 13 | በመናገር የልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 14 | በመናገር የልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | 2 | 20% | 8 | 80% |
| 15 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | 3 | 30% | 7% | 70 |

በሰንጠረዥ 4.4. የቀረበው በመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራት ተሳትፎ እና ለማሳተፍ ከተከናወኑ የክፍል ምልከታ ነጥቦች የመናገር ትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚያደርጉት የልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ መታየቱን የሚመለከት ነው። Sartika (2020) መናገርን በመማር ሂደት የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና የተለያዩ የልምምድ ተግባራትን ማድረግ በክሂላቸው መዳበር ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው። ይሁን እንጂ በክፍል ውስጥ የተደረገው የክፍል ምልከታ ውጤት እንዳመለከተው

የተማሪዎች ልምምድ እና የተማሪዎች ተሳትፎ በአራት (40%) መምህራን ጎልቶ የታየ ሲሆን፣ በስድሰት (60%) መምህራን የተማሪዎች ተሳትፎ ግልቶ ያልታየበት ነው። ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ ስድስቱ መምህራን የልምምድ ተግባራትን እንዴት መከወን እንዳለባቸው የማመቻቸትና የመምራት ሁኔታ አልታየም። ይህም ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ ከማድረግ ይልቅ ግራ እንዲጋቡ ሲያደርግ ታይተዋል። እንዲሁም ተማሪዎች ለልምምድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ አራት (40%) መምህራን ሲያበረታቱ፣ በስድሰት (60%) መምህራን ተማሪዎች ለልምምድ የተሰጣቸውን ጊዜ እንዲጠቀሙ ከማድረግ አኳያ ክፍተት ያለባቸው ናቸው። ይህም ለትምህርትነት የቀረበውን የትምህርት ይዘቱን አላማ በመግለጽ፣ የሚያስቡበትን፣ መረጃ የሚያደራጁበትን፣ የሚለማመዱበትን እና የሚያቀርቡበት ጊዜ እንዲጠቀሙ ያለማድረግ ታይቷል።

የቋንቋ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች የተራክቦ አውድ በመፍጠር መረጃ እንዲለዋወጡና ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ሊያደርጉ ይገባል። እንደ Kayi (2006) ገለጻ፣ የንግግር ክሂል ለማስተማር የሚዘጋጁና የሚቀርቡ ተግባራት አሉ። እነዚህም ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውት፣… ወዘተ ሲሆኑ፣ የተራክቦ አውድ በመፍጠር ተማሪዎች እንዲለማመዱ እና እንዲሳተፉ በማድረግ ይከናወናል። ከዚህ በመነሳት የመናገር ክሂልን መለማመድ የሚያስችሉ ተግባራት (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ቀርበው ስለመከናወናቸው በምልከታ ተፈትሾ አምስት (50%) መምህራን ያከናወኑ ሲሆን፣ አምስቱ (50%) መምህራን አላከናወኑም። እንዲሁም እነዚህን የማስተማሪያ ዘዴዎችበልምምድ ሂደቱ ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ እና በቡድን የመማር ምርጫ ተግባራዊ መደረጉ በምልከታ ለማረጋገጥ ተሞክሯል። በዚህ መሰረት ሰባት (70%) መምህራን ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው ተማሪዎች ተግባራትን እንዲከናወኑ ያደርጉ ነበር። በአንጻሩ ሶስቱ (30%) መምህራን ይህን አላደረጉም። ይህም የመምህራን የክፍል ውስጥ የመማር ሂደት ተማሪ ተኮር ገለጻ ላይ ማተኮሩን ያመለክታል።

በመማሪ ክፍል ውስጥ መምህራን ለማስተማር ሲመጡ ከተማሪዎች ችሎታ ከፍ ያለ ችሎታ እና የተሻለ አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል። ይህም ችሎታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የትኛው/ዋ ተማሪ አይን አፋር መሆኑን/ኗን በመለየት ለእነርሱ ተገቢውን እንክብካቤና ጥንቃቄ ለማድረግ

ይጠቅማል። እነዚህን አይነት ተማሪዎች በመናገር ወቅት እንዲሳተፉ ለማድረግ በክፍል ውስጥ ለመናገር የሚችሉ ተማሪዎችን ማስቀደም፣ በመቀጠል ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች ሃሳብ እንዲሰጡ ማድረግ እና የሚፈሩ ወይም የሚፈር ሁኔታ የሚታይባቸውን እንዲናገሩ በመጋበዝ ማደፋፈር ያስፈልጋል። እንዲሁም ለእንደዚህ አይነት ተማሪዎች ምቹ አውድ ማዘጋጀት፣ እንዲናገሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ በጥንድና በቡድን ማሰራትና ማናገር ይመከራል። ቢሆንም ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት መናገር እንዲለማመዱ ለማበረታታት አኳያ የክፍል ምልከታ ውጤት አምስት (50%) መምህራን የሚያበረታቱ ሲሆን፣ አምስቱ (50%) መምህራን እያበረታቱ አልነበረም።

መምህራን በክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ሲሰጡ የልምምድ ተግባራት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀማቸውን በተመለከተ በክፍል ምልከታ ወቅት ሁለት (20%) መምህራን ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን በማሰራት የልምምድ ተግባራት በውስን ተማሪዎች እንደይያዙ የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ፣ ሰባት (70%) መምህራን ግን ብዙም ትርጉም አልሰጡም። ይህም ተማሪዎችን ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ላይ ተሸሸበ እንዲሆንና ሌሎችን ያለማሳተፍ በተማሪዎች ላይ እንዲመጣ የሚፈለገው የመናገር ክሂል መሻሻል እንዳይታ ሊደርግ ይችላል። እንዲሁም ተማሪዎች እርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ከማድረግ አኳያ በክፍል ምልከታ ጊዜ አራት (40%) መምህራን ተማሪዎች በልምምድ ወቅት እንዲወያዩና እንሳተፉ ሲያደርጉ ሌሎች ስድስት (50%) መምህራን ይህን አላደረጉም። Harmer (2007) እንደገለጹት፣ የመናገር ክሂል ትምህርት ውይይት ዘዴ ማስተማር የተለመደ ነው። በዚህ ዘዴ ተማሪዎች ሳይጨናነቁ እንዳቸው ከአንዳቸው ጋር ሃሳብ ይለዋወጣሉ። ለዚህም መምህራን ክፍል ውስጥ ቡድን በማደራጀት ሊያሰሩ ይገባል። ይሁን በስድስት መምህራን ይህ አልታየም።

በመናገር የልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል በመምህራን ስለመሰጠቱ በክፍል ምልከታ ወቅት ለመፈተሸ ተሞክሯል። በዚህ መሰረት ሁለት (20%) መምህራን ተማሪዎች እንዲናገሩ እና በልምምድ እንዲያደርጉ እድል ይሰጡ ነበር። ቀሪ ስምንት (80%) መምህራን ይህን አልታየባቸውም። ተማሪዎቸ በልምምድ ወቅት ሲሳሳቱም ለማረም የሚያደርጉት ጥረት በሶስት (30%) መምህራን ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ሰባት

(70%) መምህራን ይህን ስያደርጉ አልታዩም። ይህም መምህራን የመናገርን ክሂል ለማስተማርና ተማሪዎች በክሂሉ መሻሻል እንዲሳዩ ለማድረግ የሚሰሩት ስራ ደካማ መሆኑን ያሳያል።

በመምህራን ተግባራዊ ይደረግ የነበረው የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራት ተሳትፎ እና የማሳተፍ ክንውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘውን መረጃዎች ትንተና ለማመሳከር ለተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ በማሰራጨት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል። እንደሚከተለውም ይቀርባሉ።

ሰንጠረዥ 4.5. በመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራት ተሳትፎ እና የማሳተፍ ክንውን የተማሪዎች ምላሽ መረጃዎች ትንተና

| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ሲቀርብ ተግባራት በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ ማከናወን በሚያስችለኝ መልኩ ይቀርባል። | 24 | 19.36% | 31 | 25% | 27 | 21.77 % | 19 | 15.3 2% | 23 | 18.55% |
| 6 | መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን በማከናውንበት ወቅት እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታቱኛል። | 27 | 21.77% | 32 | 25.81% | 20 | 16.13 % | 21 | 16.9 4% | 24 | 19.35% |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው። | 34 | 27.42% | 30 | 24.19% | 23 | 18.55 % | 21 | 16.9 4% | 16 | 12.9% |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ሚና ነበራቸው። | 36 | 29.03% | 35 | 28.23% | 19 | 15.32 % | 21 | 16.9 4% | 13 | 10.48% |
| 10 | የመናገር ተግባራትን ሳከናውኑ ሀሳቤን በነፃነት እገልጻለሁ። | 46 | 37.1% | 53 | 42.74% | 14 | 11.29 % | 6 | 4.84 % | 5 | 4.03% |
| 11 | መምህራን በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም እድል ይሰጡናል። | 14 | 11.29% | 17 | 13.71% | 35 | 28.23 % | 31 | 25% | 27 | 21.77% |
| 12 | በመናገር ትምህርት የመማር ሂደት በትግበራ ወቅት ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ። | 29 | 23.39% | 37 | 29.84% | 28 | 22.58 % | 18 | 14.5 1% | 12 | 9.68% |
| 13 | የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣቸዋል። | 17 | 13.7% | 13 | 10.48% | 38 | 30.65 % | 35 | 28.2 3% | 21 | 16.94% |

በሰንጠረዥ 4.5. የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ሲቀርብ ተግባራት በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ. ማከናወን በሚያስችለኝ መልኩ መቅረቡን በተመለከተ በጣም እስማማለሁ 24 (19.36%)፣ እስማማለሁ 31 (25%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 27(21.77%) አልስማማም 19(15.32%) እና በፍጹም አልስማማም 23(18.55%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የትንተናው ውጤት በበጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 44.36 በመቶ ሰሆን፣ ይህም የመናገር ክሂል ተግባራት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተለያዩ የመማር ምርጫዎች ላይ ያለመመስረታቸውን ያመለከታል። በክፍል ምልከታ ወቅት ከታየው ውጤትም ጋር ይቃረናል። ስለሆነም በተለያዩ ጊዜያት መምህራን ይህን ተግባራዊ አላደረጉም ይሆናል። እንዲሁም መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ… የመናገር ክሂል ተግባራትን ተማሪዎች ሲያከናውኑ እየተዘዋወሩ በመከታተላቸውንና ማበረታታቸውን በተመለከተ ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በጣም እስማማለሁ 27 (21.77%)፣ እስማማለሁ 32 (25.81%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 20(16.13%) አልስማማም 21(16.94%) እና በፍጹም አልስማማም 24(19.35%) ሆኗል። ይህም ውጤት በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ… ከማሰራት አኳያ ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል።

በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የመናገር ክሂል ትምህርት በተማሪዎች የመማር የሚመሰረት፣ ከተማሪዎች ነባራዊ ህይወት ጋር የሚያያዝ እና በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የሚለማመዱት ሊሆን ይገባል። በዚህ መሰረት በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ የመናገር ክሂል ተግባራት ከተማሪዎች የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ለመፈተሽ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። በጣም እስማማለሁ 34(27.42%)፣ እስማማለሁ 30(24.19%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 23(18.55%) አልስማማም 21(16.94%) እና በፍጹም አልስማማም 16(12.9%) የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ውጤቱም ለተማሪዎች የሚቀርበው የንግግር ትምህርት ባብዛኛው ከተማሪዎች የህይወት ልምድ ጋር ያልተቆራኙ መሆናቸው አረጋግጧል።

የማስተማሪያ ዘዴዎች (የንግግር፣ የጭውውት፣ የክርክር የውይይት ስርአት) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ የተማሪዎች ክሂል እንዲዳብር ከማድረግ አኳያ የነበረውን ሚና ለመመርመር ጥያቄ ቀርቦላቸው፤ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ 36(29.30%)፣ እስማማለሁ 35(28.23%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 19(15.32%) አልስማማም 21(16.94%) እና በፍጹም አልስማማም 13(10.48%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የጥናቱ ውጤት መምህራን እነዚህን የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሰጡት ትኩረት ቢኖርም አናሳ መሆኑን ያሳያል።

ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ ነጻነት የሚሰጣቸውን መሆነን ለማረጋገጥ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። የተማሪዎችም ምላሽ በጣም እስማማለሁ 46(37.1%)፣ እስማማለሁ 53(42.74%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 14(11.29%) አልስማማም 6(4.84%) እና በፍጹም አልስማማም 5(4.03%) ሆኗል። ውጤቱም በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ የተሰጠው ውጤት 79.84 ነው። ይህም ለመናገር ክሂል ማስተማሪያነት ተግባራት ሲሰጡ ተማሪዎች ለመናገር ነጻነት የሚሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በመናገር ሂደት በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህቶችን መምህራን በቀጥታ ከማረም ይልቅ ተማሪዎች እርስ በርስ እንድተራረሙ እድል ስለመስጠታቸው ጥያቄ ቀርቦላቸው ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ 14(11.29%)፣ እስማማለሁ 17(13.71%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 35(28.31%) አልስማማም 31(25%) እና በፍጹም አልስማማም 27(21.77%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ጥያቄውን ከመስማማት አኳያ 14(11.29%) ተማሪዎች በጣም መስማማታቸውንና 17(13.71%) 35(28.2%) አልስማማም 31(25%) እና በፍጹም አልስማማም 27(21.77%) በሚል ምላሽ ሰጥተዋል። 25 % ተማሪዎች በጥያቄው መስማማታቸውን የገለጹ ሲሆን ይህም የሚያሳየው መምህራን በተማሪዎች የሚፈጸሙ የንግግር ወቅት ስህተቶች ለማረም ለተማሪዎች እድል የማይሰጡና በራሳቸው ብቻ የሚያርሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

በክፍል ውስጥ አንዳንድ ተማሪዎች ለመናገር ይፈራሉ። መምህራን እነዚህ ተማሪዎች ከሌሎች እኩል እንዲሳተፉ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ይሁን እንጂ መምህራን በመናገር ትምህርት

የመማር ሂደት በትግበራ ወቅት ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ስለማበረታታቸው ጥያቄ ቀርቦላቸው በጣም እስማማለሁ 29(23.39%)፣ እስማማለሁ 37(29.84%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 28(22.58%) አልስማማም 18(14.51%) እና በፍጹም አልስማማም 12(9.68%) የሚል ምላሽ ተማሪዎች ሰጥተዋል። ይህም ውጤት 53.23 በመቶ ሲሆን፣ መምህራን አይን አፋር ወይም ፈሪ ተማሪዎች ለማሳተፍ ያደረጉት ጥረት ከአማካይ ብዙም ያልዘዘለ መሆኑን ያመለክታል።

የመናገር ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ከመስጠትም ያለውን ሁኔታ ለመፈተሽ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ምላሻቸው በጣም እስማማለሁ 17(13.7%)፣ እስማማለሁ 13(10.48%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 38(30.65%) አልስማማም 35(28.23%) እና በፍጹም አልስማማም 21(16.94%) ሆኗል። ይህም ውጤት በክፍል ውስጥ የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት የተሳትፎ ድርሻ ዝቅተኛ (24.18 በመቶ ብቻ) ነው።

ሰንጠረዥ 4.6. በመምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራት ተሳትፎ እና የማሳተፍ ክንውን የመምህራን ምላሽ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | ሁልጊዜ | | አብዛኛው ጊዜ | | አንዳንዴ | | ጨርሶ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 6 | በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ከህይወት ገጠመኝ ጋር እንዲተሳሰሩ እና እንዲለማመዱ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 6 | 60% | 2 | 20% | - | |
| 7 | በመናገር ሂደት የራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀትና ችሎታቸውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታለሁ። | 3 | 30% | 4 | 40% | 3 | 30% | - | |
| 8 | በክፍል ውስጥ መናገር በመማር ሂደት የተሳትፎ ጉድለት ያላባቸው፣ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ ብልሃቶችን አመቻቻለሁ። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |
| 9 | የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ (አለማምዳለሁ)። | 1 | 10% | 3 | 30% | 6 | 60% | - | |

በሰንጠረዥ 4.6. የቀረበው የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው መምህራን በክፍል ውስጥ ለመናገር ክሂል ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ሲመርጡ ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ከህይወት ገጠመኝ ጋር እያስተሳሰሩ ስለመለማመዳቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለት (20%) መምህራን ሁልጊዜ፣ ስድስት (60%) አብዛኛውን ጊዜ እና ሁለት (20%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ የሚያከናውኑ መሆናቸው አረጋግጠዋል። ይሁን እንጂ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ከተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ታይቷል።

መናገር አንድ ሰው ስለተሰማውና ስለታዘበው ነገር ያለውን እውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ ሐሳቡን በማደራጀት ለአድማጮ የሚያቀርብበት ክሂል ነው። ስለሆነም መምህራን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ጥያቄ ቀርበላቸው ሶስት (30%) መምህራን ሁልጊዜ፣ አራት ( 40%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እና ሶስት (30%) መምህራነ አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች በመናገር ሂደት የራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀትና ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ማድረጋቸውን ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ውጤት 30 በመቶ መምህራን ተማሪዎች የቋንቋ እውቀታቸውንና ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ለማድረግ ትኩረት ያልሰጡ መሆናቸውን አመላክቷል።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚመጡ ተማሪዎች ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎች የተሳትፎ ችግር ያለባቸውና ሀሳባቸውን በድፍረት መግለጽ የማይደፍሩ ናቸው። እነዚህን ተማሪዎች ለመርዳት መምህራን የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ለመምሀራን በክፍል ውስጥ መናገር በመማር ሂደት የተሳትፎ ጉድለት ያላባቸው፣ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ የትግበራ ብልሃቶችን ስለማመቻቸታቸው ተጠይቀው ሁለት(20%) መምህራን ሁልጊዜ፣ አምስት (50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እና ሶስት (30%) መምህራን እንዳንድ ጊዜ እንደሚያመቻቹ ገልጸዋል። ይህም ውጤት ሁሉም መምህራን ሁሉም ተማሪዎች በማነገር ተግባራት እኩል እንዲሳተፉ ያለማድረጋቸውን ያመለክታል።

ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ተተኳሪውን እና ሌሎችን ክሂሎች ለማዳበር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም መምህራን የመናገርን ክሂል ከሌለች ክሂሎች ጋር አቀናጀተው ስለማስተማራቸውና ስለማለማመዳቸው ተጠይቀው አንድ (10%) መምህር ሁልጊዜ፣ ሶስት (30%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እና ስድስት (60%) መምህራን አቀናጅተው እንደሚያስተምሩና

እንደሚያለማምዱ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ውጤቱም መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው ከማስተማር አኳያ ምንም ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውን አመላክቷል።

በአጠቃላይ ከክፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎችና መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እንዳመለከተው መምህራን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ በልምምድ ተግባራት ተማሪዎችን ከማሳተፍ እና ኃላፊነት ወስደው እንዲማሩ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ጉድለት የታየበት ስለሆነ ትኩረት መስጠት ይጠይቃል። በተለይ በመማሪያ ክፍሉ የሚታየውን ንግግር ለማስተማር ተግባራዊ የሚደረገው ገለጻ ተኮር ዘዴ ማረም አስፈላጊ ነው።

### 4.1.3 የተማሪዎች በክፍል ውስጥየመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት መምህራን የልምምድ አውድ አዘግጅቶና የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀም

የዚህ ጥናት ሰስተኛው ጥያቄ በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ? የሚል ነው። ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ከክፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎች እና መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል።

ሰንጠረዥ 4.7. በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ስለመጠቀማቸው ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ትግበራ ዘዴ | የምላሽ አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | በመቶኛ | አይ | በመቶኛ |
| 16 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | 1 | 10% | 9 | 90% |
| 17 | የመናገር ትምህርት ሂደት የንግግር ማስተማሪያ ተግባራት ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባቡ በሚያስችል ዐውድ ተዘጋጅተው የተከናወኑ ነበር? | 3 | 30% | 7 | 70% |
| 18 | የመናገር ዓላማ ግብ እንዲመታ ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የመናገር ተግባር እንዲከናወኑ ተደርጓል? | 6 | 60% | 4 | 40% |
| 19 | መናገር ለማስተማር የተሰጡት ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 20 | ተማሪዎች በመናገር ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት እርማቱ ወዲያው ይሰጥ ነበር? | 3 | 30% | 7 | 70% |

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል ለማስተማር ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁና የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። በዚህ መሰረት በሰንጠረዥ 4.7 በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ የሚያስችል አውድ መዘጋጀቱን በተመለከተ በክፍል ምልከታ ሲፈተሽ አንድ (10%) መምህር የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ ተግባራዊ ሲያደርግ፣ ዘጠኝ (90%) መምህራን አላከናወኑም። ይህም ውጤት መምህራን የመናገርን ክሂል ለማስተማር በክፍል ውስጥ የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን የማያቀርቡ መሆናቸውን አመላክቷል፡ ፡ በተጨማሪ የመናገር ዓላማ ግብ እንዲመታ ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የመናገር ተግባር እንደሚያከናወኑ በክፍል ምልከታ ተፈትሾ፤ ስድስት (60%) መምህራን የውይይትና የክርክር አውድ በማቅረብ የሚያስተምሩ ሲሆን፣ አራት (40%) መምህራን ይህን ሲያደርጉ አልታዩም። በተጨማሪ እነዚህ በመምህራን ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ሰለመሆናቸው በተደረገው የክፍል ምልከታ አምስት (50%) መምህራን ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የፈለጉት ነገር ፈጽመው ታይተዋል። ቀሪ አምሰት (50%) መምህራን ያመጧቸው ተግባራት በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አልተደረጉም። ከውጤቱም መረዳት የሚቻለው ሶስቱ መምሀራን አላማቸውን ሲያሳኩ፣ ሌሎች ሰባቱ ያላሰኩ መሆናቸውን አረጋግጧል።

ለተማሪዎች በመናገር ክሂል ማስተማሪያነት የሚቀርቡ አውዶች በቀላሉ እና በነጻነት ተግባራዊ የሚደረጉ መሆን አለባቸው። አውዶችን ሲለማመዱ ተማሪዎች የሚጨነቁ ከሆነ ለመስራት አይነሳሱም። ስለሆነም በአውድ ምርጫ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ጥሩ ነው። ከዚህ ጽንሰ-ሃሳብ በመነሳት መምህራን የመናገር ትምህርት ሂደት የንግግር ማስተማሪያ ተግባራት ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባቡ በሚያስችል ዐውድ አዘጋጅተው ስለማከናወናቸው በክፍል ምልከታ ተረጋግጦ፤ በሶስት (30%) መምህራን የቀረቡ አውዶች ተማሪዎች በቀላሉ እና በነጻነት ተግባራዊ ያደረጓቸው ሲሆን፣ በሰባት (70%) መምህራን የቀረቡ አውዶች ተማሪዎች በቀላሉ እና በነጻነት ተግባራዊ ማድረግ ያልቻሏቸው ናቸው። ይህም ውጤት መምህራን ጊዜ ወስደው የማስተማሪያ አውድ የማያዘጋጁ መሆናቸውን ያመለክታል። በተጨማሪ የመናገር ዓላማ ግብ እንዲመታ

ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የመናገር ተግባር እንደሚያከናወኑ በክፍል ምልከታ ተፈትሾ፤ ስድስት (60%) መምህራን የውይይትና የክርክር አውድ በማቅረብ የሚያስተምሩ ሲሆን፣ አራት (40%) መምህራን ይህን ሲያደርጉ አልታዩም። በተጨማሪ እነዚህ በመምህራን ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ሰለመሆናቸው በተደረገው የክፍል ምልከታ አምስት (50%) መምህራን ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የፈለጉት ነገር ፈጽመው ታይተዋል። አጥኚዉ በትምህርት ቤቶቹ በስራ ካሳለፈዉ ጊዜና ልምድ አኳያ ሁሉም የክፍል ደረጃዉ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ ቢሆኑም የቀሪ አምሰት (50%) መምህራን ያመጧቸው ተግባራት በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አልተደረጉም።

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን ተማሪዎች በመናገር ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት እርማቱ ወዲያው መስጠት አለመስጠታቸውን በተመለከተ የክፍል ምልከታ ተደርጓል። ውጤቱም አምስት (50%) መምህራን በተማሪዎች ንግግር ወቅት የተፈጸሙ ስህተቶችን ወዲያውኑ ሲያርሙ፤ ቀሪ አምሰት (50%) መምህራን ስህተት ከማረም ይልቅ በቁጣ ይናገሯቸው ነበር። ይህም ተማሪን ከመርዳት ይልቅ ግራ ሲያጋባ ተስተውሏል።

ሰንጠረዥ 4.8. በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ስለመጠቀማቸው ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የመናገር ትምህርት በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባር ይቀርብላችሁ ነበር። | 29 | 23.39 % | 33 | 26.61 % | 27 | 21.77% | 18 | 14. 52% | 17 | 13.71 % |
| 14 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ አውድ ተዘጋጅቶላችሁ ይቀርብ ነበር። | 31 | 25. | 34 | 27.42 | 29 | 23.39 | 13 | 10. 48 | 17 | 13.71 |

የመናገር ትምህርት በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱ ስለመቅረቡና የተማሪዎች ክሂል እንዲዳብር ከማገዝ አኳያ ያለውን ሁኔታ ለመፈተሽ

ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ምላሻቸው በጣም እስማማለሁ 29 (23.31%)፣ እስማማለሁ 33 (26.61%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 27(21.77%) አልስማማም 14(14.52%) እና በፍጹም አልስማማም 17(13.71%) ሆኗል። ውጤቱ የሚያስረዳን በመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት አፈጻጸም በመምህራን የበላይነት የሚመራ ተማሪዎች እንዲለማመዱ የማይደረጉበት መሆኑን ነው። እንዲሁም ተማሪዎች የስዕሎችንና ፎቶግራፎችን ቅደም ተከተላዊ ሁኔታ ተመልክተው ተማሪዎች ሃሳባቸዉን እንዲገልጹ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ ለተማዎች ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። የሰጡት ምለሽ በጣም እስማማለሁ 31(25%)፣ እስማማለሁ 34 (27.42%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 29(23.39%) አልስማማም 13(10.48%) እና በፍጹም አልስማማም 17(13.71%) ሆኗል። የዚህ መረጃ ትንተና ውጤት የበጣም እስማማለሁ እና እሰማማለሁ 52.42 በመቶ እንዳመለከተው የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ አውድ አዘጋጅተው ተማሪዎች እንዲለማመዱ የማድረግ ስራ ከአማካይ ያላለፈ ነው።

ሰንጠረዥ 4.9. በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ስለመጠቀማቸው የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | ሁልጊዜ | | አብዛኛው ጊዜ | | አንዳንዴ | | ጨርሶ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 10 | የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የማስተማሪያ ብልሃችን (የሚታዩ ነገሮችን ስዕል፤ ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ) በመጠቀም እንዲለማመዱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 11 | ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ትምህርት በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ አውድ አመቻቻለሁ። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |

የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የማስተማሪያ ብልሃችን (የሚታዩ ነገሮችን ስዕል ፤ ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ) በመጠቀም እንዲለማመዱና እንዲናገሩ ስለማድረጋቸውም ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለት (20%) መምህራን ሁልጊዜ፣ ሶስት (30%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እና አምስት (50%) መምህራን እንዳንድ ጊዜ የማስተማሪያ ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ በመምህራን ገለጻ መያዙን

ያረጋግጣል። በተጨማሪ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ትምህርት በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ አውድ ከማመቻቸት አኳያ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለት(20%) መምህራን ሁልጊዜ፣ አምስት (50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እና ሶስት (30%) መምህራን እንዳንድ ጊዜ በቡድን ሆነው ሃሳብ እንዲለዋወጡ አወድ እንደሚያመቻቹ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ውጤቱም ለተማሪዎች በቂ የልምምድ አውድ የሚያመቻቹ መምህራን 70 በመቶ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ፣ ሌሎች የሰጡት ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ ከክፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎች እና ከመምህራን ተሰብስበው የተተነተኑ መረጃዎች በንግግር ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት የመምህህራን አቀራረብ፣ ተማሪዎችን እንዲሳተፉና እንዲለማመዱ እና አውድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ መምህራን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ የሚያሳስብ ነው።

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፈተሽ ነዉ። ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ ምን ይመስላል?፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርትን አተገባበር ወቅት የልምምድ ሂደቱ ምን ይመስላል? እና በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ? የሚሉ ናቸው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ጥያቄዎችን ለመመለስ መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ምልከታ መረጃዎች ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ በገለጻ ስልት ተብራርተዋል። ውጤቱም በተወሰኑ መምህራን ንግግር ለማስተማር ተግባራዊ ለሚደረጉ የማስተማሪያ ዘዴዎች ትኩረት አለመስጠታቸው፣ በመማሪያ ክፍል ከመምህራን ገለጻ ባለፈ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲተገበር አለመደረጉ፣ ተማሪዎችን ለማነቃቃት መሰራት የነበረባቸው ተግባራት መረሳታቸው፣ የአውድ ዝግጅት ትኩረት አለመሰጠቱ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል ያለማሳተፍ እና ሁሉም ተማሪዎች በተለይ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ የማድረጉ ስራ ትኩረት ማጣቱ እና የሚመረጡ የንግግር ማስተማሪያ

ርዕሶች ከተማሪዎች የእለት ተእለት ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር የማጣጣም ስራ አለመሰራቱን አረጋግጧል።

የዚህ ጥናት ግኝት ከሰለሞን (2010 ዓ.ም) እና እጅጉ (2003 ዓ.ም) ጋር ይስማማል። ሰለሞን (2010 ዓ.ም) የጥናታቸው ትኩረት የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው በተመረጡ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ ተሳታፊዎች የእነዚህ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። የጥናቱም መረጃዎች ከተሳታፊዎች በክፍል ምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅ እና በቃለመጠይቅ ተሰብስበው ተተንትነዋል። የጥናቱም ውጤት በተወሰኑ መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸውን፣ በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር ሀሳባቸውን በነፃ የሚገልጹበትን ሁኔታ አለማመቻቸታውን፣ የመናገር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ በተጨማሪም ከመማ ሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ የዕለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ርእሰ ጉዳይ ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል አለመስጠቱ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት የተሻለ ሙከራ አለመደረጉ አመላክቷል። ስለዚህ የጥናት ውጤት ከተተኳሪው ጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል።

እጅጉ (2003 ዓ.ም) በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ላይ የተደረገ ግምገማዊ ጥናት ነው። በመማሪያ ክፍል ውስጥ የነበረውን አጠቃላይ አተገባበር ገምግመው ይፋ ያደረጉት ውጤት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ተግባራዊ መደረግ የነበረባቸው ብልሃቶች አለመከናወናቸውን ገምግሟል። በተለይ በቡድን ውይይት፣ የግል፣ የጥንድ ወዘተ ማቅረቢያ ዘዴዎችን መምህራን መተግበር አለመቻላቸውን፣ የተማሪዎች ተራክቦ እኩል እንዳልሆነና የተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት አለመተከሩ እና የትግበራ ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች ያሳተፈ አለመሆኑን አረጋግጠዋል። ስለሆነም የዚህም ጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት ጋር ይስማማል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፈተሽ ነዉ። ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ይመስላል? ፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርትን አተገባበር ወቅት የአቀራረብ ሂደቱ ምን ይመስላል? እና በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት መምህራን የልምምድ አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ያስተምራሉ? የሚሉ ናቸው።

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ጥያቄዎችን ለመመለስ መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ምልከታ መረጃዎች ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ በገለጻ ስልት ተብራርተዋል። ውጤቱም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለንግግር ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ትኩረት ያልሰጡ መሆናቸው፣ በተማሪ ተኮር አቀራረብ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ትብብራዊነት በተማሪዎች መካከል እንዲታይ ያለማድረጋቸው፣ ተማሪዎችን ለማነቃቃት መሰራት የነበረባቸው ተግባራት መረሳታቸው፣ የአውድ ዝግጅት ትኩረት የይድረስ መሆኑ፣ ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርቱ እኩል ያለማሳተፍ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ያለማድረግ እና የሚመረጡ የንግግር ማስተማሪያ ርዕሶች ከተማሪዎች የእለት ተእለት ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር የማጣጣም ስራ አለመሰራቱን ተመላክቷል። በአብዛኛው የታዩ ክፍተቶች ከመምህራን ትኩረት ማነስ የመጡ ስለሆነ መምህራን ለተማሪዎች የመማር ውጤት እና ለውጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሊያስተውሉ ይገባል።

## 5.2. አስተያየት

የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበርና አቀራረብ፣ የልምምድ ሂደቱ እና አውድ አዘጋጅተውና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው ከማስተማር አኳያ የታዩ ክፍተቶች በጥናቱ ውጤት ተገልጸዋል። ከዚህ የጥናት ውጤት በመነሳት የሚከተለው አስተያየት ተሰጥቷል።

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ትምህርት ለማስተማር ሲዘጋጁ የዕለቱን የትምህርት ይዘት አላማ በመግለጽ እና ተማሪዎችን ለዕለቱ ትምህርት እንዲዘጋጁ በማነቃቃት ወደ ሌሎች ተግባራት መሸጋገር ቢችሉ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

- የተማሪዎችን የመማር ምርጫ ለመጠበቅ እንዲመች ለልምምድ የሚዘጋጁ ተግባራት በግል፣ በጥንድ እና በቡድን መማር ላይ ቢያተኩሩ ይመረጣል፡፡ ምክንያም ተማሪዎች በትብብራዊነት ላይ የተመሰረተ መማር ቢለምዱ በመናገር ሂደት በነጻነት ሃሳባቸውን መግለጽ ይለማመዳሉ፡፡

- በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የንግግር ክሂል ከሆነ ሁሉም ተማሪዎች እንዲናገሩ እኩል እድል መስጠት እና ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች ችግራቸውን በማወቅና በቡድን ስራ እንዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆን የንግግር አላማ ሊሳካ ይችላል፡፡

- በተቻለ መጠን የቋንቋ መምህራን የመናገር ትምህርት አውድ ሲያጋጁ ተማሪዎች ፈጠራን እንዲለማመዱ የሚያስችላቸውን አውድ ቢያዘጋጁ እና በሚስማማ የማስተማሪያ መሳሪያ ማቅረብ ቢቻል ይመረጣል፡፡

- የመናገር ትምህርት ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያ ይዘቶች ሲዘጋጁ የተለያዩ የማስማሪያ ዘዴዎች እና ብልሃቶች ተካተው ለልምምድ ቢቀርቡ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማሻሻል ይቻላል፡፡

- ባለድርሻ አካላት በመምህራን የሚታየውን የትግበራ ችግር ለመቅረፍ አስፈላጊ ናቸው፤ የተባሉ ስልጠናዎች በማዘጋጀት ስልጠና ቢሰጣቸው የተሻለ ነው፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


መንግስቱ ታደሰ። (1997) ። "በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ (ያልታተመ) ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ።

ማረው አለሙ። (1998) ። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ማረው አለሙ እና ሰፋ መካ። (1999) ። "በሙያ መስክ ማስተማር (ያልታተመ) ።" ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባሀር ዳር።

ሰለሞን ገብሩ። (2010 ዓ.ም) ። "በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጥናት) ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ።

በድሉ ዋቅጅራ። (1996) ። *በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር* ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

_________ ። (2007) ። *በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር።* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬድንግ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ሸዋዬ። (1981) ። "ሥነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር (ያልታተመ) ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ።

ታደሰ ሲባሞ። (2004) ። "አማርኛን የማስተማር ስነዘዴ II (ያልታተመ) ።"ትምህርት ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ።

አያልሰው ይታየው (2003)። "ከ 9 ኛ እስከ 12 ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ በሚገኙ የልበወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመ ናገር ኪሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና እና ግምገማ (ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት)።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም።

አዘነ ደምሴ (2003 ዓ.ም) ። "{የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ፣ በአማራ ክልል፣ በሰሜን ሸዋ ዞን በሞረትና ጅሩ ወረዳ በተመረጡ ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ማሳያነት (ያልታተመ የምረቃ ጥናት) ።" ደብረ ብርሃን ዩኑቨርሲቲ፣ ደብረ ብርሃን።

እጅጉ ይማም። (2003)። "በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፈል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አመቀራረብ ግምገማ (ያልታተመ የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ)።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም።

የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት። (2004 ዓ.መ) ። *አጠቃላይ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ*። አዲስ አበባ፣ ት·መ·ማ·ማ·ድርጅት።

ፅጌ ታፈሰ። (1994) ። "ክሂሎችን የማዳበር ስነ ዘዴ (ያልታተመ) ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ።

Atkins, J .Hailom B. and Nuru, M. (1995). *Skills Development Methodology Part I*. Addis Ababa: Addis Abeba University.

Brown, H. (1980). *Principles of Language Learning and Teaching*. Prentice Hall Ine. Las Angeles: Sage Publications.

_________. (2007). *Principles oF Language Learning and Teaching*. (5thed). White Plains, NY: Pearson Education.

Brown, G. and Yule, G. (1983).*Teaching The Spoken Language*. Cambridge: Cambridge University Press.

Burns, A. (2006). *Teaching Speaking*: A Text-based Syllabus approach. Incurrent trends in the

Development and Teaching of the Four Language Skills, Esther Uso-Juan, and Alicia Martinez- Flor (eds.) Berlin: Mouton de Gruyter.

Bygate, M. (1987). *Speaking.* New York: Cambridge University press

_______. (2001). *Speaking*. The Cambridge Guide to Teaching English to Speakers of Other Languages, New York: Cambridge University Press.

_______. (2002). *Speaking* .In The Oxford hand Book of Applied Linguistics. Oxford: Oxford University press.

________. (1987). *Teaching For Class Room Interaction*. London; Longman. Group UK Limited.

________. (1992).*Teaching Oral English*. Long man Hand Book for Language Teachers. Cambride: Cambridge University Press.

Cameron, (2001). *Teaching Language to Young Learners*. Cambridge:

Cambridge University Press.

________. (2001).*Teaching English as a Second or Foreign Language* (3rd ed). USA: Heinle & Heinle.

Dornyei, I. (2001). *Motivational Strategies in the Language Classroom;* Boston Heinieman Press.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. London; Longman.

--------------- (2007).*The Practice of English Language Teaching*. (4th ed) Longman Handbooks for Language Teachers.

Jack C. Richards (2013). *Creativity in Language Teaching*. City University of Hong Kong.

Kayi, H. (2006). Teaching Speaking: Activities to Promote Speaking in a Second Language. *The Internet TESL Journal,* Vol. XII, No. 11.

Little Wood, W. (1981). *Communicative Language Teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Malay, A. and Duff, A. (1978). *Drama Techniques in Language Learning*. Cambridge: Cambridge University press.

McDonough, J. and Shaw, C. (1993). "Materials and Methods in ELT: A Teachers Guide" Applied Language Studies, Edited by D. Crystal and K. Johnson Oxford UK and Cambridge USA: Blackwell.

Nguyen Lam Minh Tuyen (2021). "A Study on Difficulties and Solutions in English Speaking 2 Skills of Students at Hufi 3." University of Food Industry, Ho Chi Minh.

Nerfi Istianti (2013). "The correlation between student's motivation in learning speaking and their speaking ability." Jakarit University. Jakarit.

Nunan, D. (1989). *Designing Tasks for the Communicative Classroom*. Cambridge University Press.

Pahuja, N. (2001).*Teaching Speaking*. New Delhi: Animal Publications LTD.

Richards, J.C. (2008). *Teaching Speaking and Listening*. From theory to Practice; Cambridge: Cambridge University press

Sandra, J. (2002). *Interpreting Communicative Language Teaching*.Contexts and Concerns in Teaching Education; London: Yale University press.

Sartika Andi Patau (2020). *Factors That Influence Students' Participation In English Speaking Classroom Activities*. Sintuwu Maroso University.

Scrivener, j. (1994). *Learning Teaching*. Oxford: Heineman.

Staab, C. (1992). *Oral Language for Today's Classroom*. Markham, ON: pippin Publishing.

Thanyalak, O. (2012). "Developing Speaking Skills Using Three Communicative Activities." *International Journal of Social Science and Humanity*, Vol.2, No.6.

Ur, p. (1996). *A course in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, T and etal. (2004). *Teaching Speaking, Listening and Writing*. The International Acadamy of Education; palais Des Acadamics.TYPHON Annecy Press.

# አባሪዎች

አባሪ 1. በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲሰ፤ የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ይህ መጠይቅ የተማሪዎችን በአማርኛ የመናገር ክሂል በማስተማር ሂደት ያለውን የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመፈተሽ የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ ነው።

ውድ ተማሪዎች፤

ይህ መጠይቅ በ8ኛ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመናገር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። ለመጠይቁ የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ መሳካት አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው። ስለሆነም፣ ይህ ጥናት ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ የእናንተ እገዛ ስለሚያስፈልገኝ የበኩላችሁን ድርሻ እንድትወጡ በአክብሮት አጠይቃለሁ። አስቀድሜ ጊዜ ሰጥታችሁ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ ስለሆናችሁ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ማሳሰቢያ፡ በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

ክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃ

- የትምህርት ቤቱ ስም…………….
- ፆታ ወንድ……….. ሴት…………

ክፍል ሁለት

ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ምላሽ የሚጠይቁ ዝርዝር መጠይቆች እና አምስት የምላሽ አማራጮች ተሰጥተዋል። እናንተም በጥያቄዎቹ ትይዩ ምላሻችሁን የ"X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ።

<u>የቁጥሮች ዕሳቤ</u>

5= በጣም እስማማሉ

4= እስማማለሁ

3= መወሰን እቸገራለሁ

2= አልስማማም

1= ፍጹም አልስማማም

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፍጹም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አለማው ይገለጽልኛል፡፡ | | | | | |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ማነቃቂያ ይቀርብልኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመሩ በፊት ግልፅ መመሪያ ይሰጠኛል፡፡ | | | | | |
| 4 | የመናገር ትምህርት በመማር ሂደት የተለያዩ ሞዴል ማስተማሪያ አውዶች ይቀርቡልኛል፡፡ | | | | | |
| 5 | በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ሲቀርብ ተግባራት በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ ማከናወን በሚያስችለኝ መልኩ ይቀርባል፡፡ | | | | | |
| 6 | መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን በማከናውንበት ወቅት እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታቱኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | የመናገር ትምህርት በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱ ስለሚቀርቡ ክሂሉን እንዳዳብር አግዞኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ሚና ነበራቸው፡፡ | | | | | |
| 10 | የመናገር ተግባራትን ሳከናውኑ ሀሳቤን በነፃነት እገልጻለሁ፡፡ | | | | | |
| 11 | መምህራን በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም እድል ይሰጡናል፡፡ | | | | | |
| 12 | በመናገር ትምህርት የመማር ሂደት በትግበራ ወቅት ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ፡፡ | | | | | |
| 13 | የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣቸዋል፡፡ | | | | | |
| 14 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ አውድ ተዘጋጅቶላችሁ ይቀርብ ነበር፡፡ | | | | | |

## አባሪ 2. በተማሪዎች የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | የተሰጠ ውጤት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | ፍጹም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አለማው ይገለጽልኛል፡፡ | 49 | 39.51% | 51 | 41.13% | 8 | 6.45% | 12 | 9.68% | 4 | 3.23% |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ማነቃቂያ ይቀርብልኛል፡፡ | 34 | 27.41% | 42 | 33.87% | 18 | 14.52% | 21 | 16.94% | 9 | 7.26% |
| 3 | የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመሩ በፊት ግልፅ መመሪያ ይሰጠኛል፡፡ | 53 | 42.74% | 46 | 37.1% | 11 | 8.87% | 8 | 6.45% | 6 | 4.84% |
| 4 | የመናገር ትምህርት በመማር ሂደት ፈጠራን የሚያበረታቱ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ይቀርቡልኛል፡፡ | 39 | 31.45% | 44 | 35.49% | 14 | 11.29% | 15 | 12.1% | 12 | 9.67% |

| | | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ሲቀርብ ተግባራት በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ ማከናወን በሚያስችለኝ መልኩ ይቀርባል፡፡ | 24 | 19.36% | 31 | 25% | 27 | 21.77% | 19 | 15.32% | 23 | 18.55 % |
| 6 | መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን በማከናውንበት ወቅት እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታቱኛል፡፡ | 48 | 38.7% | 52 | 41.94% | 6 | 4.84% | 11 | 8.87% | 7 | 5.65% |
| 7 | የመናገር ትምህርት በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱ ስለሚቀርቡ ክሂሉን እንዳዳብር አግዞኛል፡፡ | 29 | 23.39% | 33 | 26.61% | 27 | 21.77% | 18 | 14.52% | 17 | 13.71 % |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከህይወት ልምድ ጋር | 34 | 27.42% | 30 | 24.19% | 23 | 18.55% | 21 | 16.94% | 16 | 12.9% |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተቆራኙ ናቸው። | | | | | | | | | | |

| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ሚና ነበራቸው። | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 36 | 29.03% | 35 | 28.23% | 19 | 15.32 % | 21 | 16.94% | 13 | 10.4 8% |
| 10 | የመናገር ተግባራትን ሳከናወኑ ሀሳቤን በነፃነት እገልጻለሁ። | 46 | 37.1% | 53 | 42.74% | 14 | 11.29 % | 6 | 4.84% | 5 | 4.03 % |
| 11 | መምህራን በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም እድል ይሰጡናል። | 14 | 11.29% | 17 | 13.71% | 35 | 28.23 % | 31 | 25% | 27 | 21.7 7% |
| 12 | በመናገር ትምህርት የመማር ሂደት በትግበራ ወቅት ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ። | 29 | 23.39% | 37 | 29.84% | 28 | 22.58 % | 18 | 14.51% | 12 | 9.68 % |
| 13 | የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣቸዋል። | 17 | 13.7% | 13 | 10.48% | 38 | 30.65 % | 35 | 28.23% | 21 | 16.9 4% |
| 14 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | 31 | 25 | 34 | 27.42 | 29 | 23.39 | 13 | 10.48 | 17 | 13.7 1 |

,

አባሪ 3. የክፍል ምልከታ መጠይቅ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲሰ፤ የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ክንውን ምልከታ መከታተያ ቅፅ

- የትምህርት ቤቱ ስም…………………………….
- ምልከታ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ……………….
- ምልከታ የተደረገበት ቀን…………………………
- ምልከታ የተደረገበት ክ/ጊዜ………………………
- ምልከታ የተደረገበት ሰዓት……………………………………………..
- በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ርዕሰ……………………….

ይሀ የምልከታ ቅጽ በአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ተግባራትን የክፍል ውስጥ አተግባር በ8ኛ ክፍል ለመገምገም ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅት ተግባራቱ ተከናውነው ከሆነ “X” ምልክት "አዎ" ከሚለው ላይ ደረጋል፡፡ተግባራቱ ያልተከነናወኑ ከሆነ ደግሞ “ x” ምልክት "አይ " ከሚለው ላይ ይመለከታል፡ ፡

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ትግበራ ዘዴ | አዎ | አይ |
|---|---|---|---|
| 1 | የመናገር ትምህርት ለማስተማር ስለቀረበው ይዘት ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | | |
| 2 | በክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርቱ አቀራረብ መርሃ ትምህርቱንና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | | |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የተማዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | | |
| 4 | የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | | |
| 5 | የመናገር ትምህርቱን ለማስተማርና ለመማር በቂ የልምምድ ተግባራት ቀርበው እንዲለማመዱ እየተደረገ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | | |
| 6 | የመናገር ትምህርት ለማስተማርና ለመማር የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችና ተግባራት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | | |
| 7 | የመናገር ትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚያደርጉት የልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ ይታይ ነበር? | | |
| 8 | የመናገር ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | | |
| 9 | የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ቀርቦ ተከናውኗል? | | |
| 10 | የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን የማስተማር ስነዘዴ ተጠቅመው ነበር? | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት መናገር እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 12 | የመናገር ትምህርት ሲሰጥ የልምምድ ተግባራት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | | |
| 13 | በመናገር የልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 14 | በመናገር የልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | | |
| 15 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | | |
| 16 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | | |
| 17 | የመናገር ትምህርት ሂደት የንግግር ማስተማሪያ ተግባራት ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባቡ በሚያስችል ዐውድ ተዘጋጅተው የተከናወኑ ነበር? | | |
| 18 | የመናገር ዓላማ ግብ እንዲመታ ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የመናገር ተግባር እንዲከናወኑ ተደርጓል? | | |
| 19 | መናገር ለማስተማር የተሰጡት ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ነበር? | | |
| 20 | ተማሪዎች በመናገር ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት እርማቱ ወዲያው ይሰጥ ነበር? | | |

## አባሪ 4. የክፍል ምልከታ መጠይቅ ውጤት

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ትግበራ ዘዴ | የምላሽ አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | በመቶኛ | አይ | በመቶኛ |
| 1 | የመናገር ትምህርት ለማስተማር ስለቀረበው ይዘት ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | 6 | 60% | 4 | 40% |
| 2 | በክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርቱ አቀራረብ መርሃ ትምህርቱንና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የተማዎችን ፈጠራ የሚያበረታታ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | - | - | 100 | 100% |
| 4 | የንግግር ትምህርት ለማስተማር የቀረበው ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 5 | የመናገር ትምህርቱን ለማስተማርና ለመማር በቂ የልምምድ ተግባራት ቀርበው እንዲለማመዱ እየተደረገ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | 3 | 30% | 7 | 70% |
| 6 | የመናገር ትምህርት ለማስተማርና ለመማር የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችና ተግባራት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | 9 | 90% | 1 | 10% |
| 7 | የመናገር ትምህርት አሰጣጥ ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚያደርጉት የልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ ይታይ ነበር? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 8 | የመናገር ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 9 | የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ቀርቦ ተከናውኗል? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 10 | የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን የማስተማር ስነዘዴ ተጠቅመው ነበር? | 7 | 70% | 3 | 30% |
| 11 | ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት መናገር እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 12 | የመናገር ትምህርት ሲሰጥ የልምምድ ተግባራት በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | 2 | 20% | 8 | 80% |
| 13 | በመናገር የልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | 4 | 40% | 6 | 60% |
| 14 | በመናገር የልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | 2 | 20% | 8 | 80% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | 3 | 30% | 7% | 70 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | 1 | 10% | 9 | 90% |
| 17 | የመናገር ትምህርት ሂደት የንግግር ማስተማሪያ ተግባራት ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባቡ በሚያስችል ዐውድ ተዘጋጅተው የተከናወኑ ነበር? | 3 | 30% | 7 | 70% |
| 18 | የመናገር ዓላማ ግብ እንዲመታ ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የመናገር ተግባር እንዲከናወኑ ተደርጓል? | 6 | 60% | 4 | 40% |
| 19 | መናገር ለማስተማር የተሰጡት ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ነበር? | 5 | 50% | 5 | 50% |
| 20 | ተማሪዎች በመናገር ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት እርማቱ ወዲያው ይሰጥ ነበር? | 3 | 30% | 7 | 70% |

አባሪ 5. በመምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

ውድ መምህራን፡- ይህ መጠይቅ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እያቀረቡ እንዳለ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። ለመጠይቁ የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ መሳካት አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው። ስለሆነም፣ ይህ ጥናት ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ የእርስዎ እገዛ ስለሚያስፈልገኝ የበኩልዎን ድርሻ እንዲወጡ በአክብሮት አጠይቃለሁ። አስቀድሜ ጊዜ ሰጥታችሁ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ ስለሆናችሁ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ማሳሰቢያ፡ በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

ክፍል አንድ

አጠቃላይ ዳራዊ መረጃ፡- ከዚህ በታች በቀረበው ክፍት በታዎች መረጃዎን ይሙሉ።

1. ጾታ...................................

2. የትምህርት ደረጃ.........................................

3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ..................................

4. የአገልግሎት ዘመን.......................................................

ክፍል ሁለት

ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ምላሽ የሚጠይቁ ዝርዝር መጠይቆች እና አራት የምላሽ አማራጮች ተሰጥተዋል። እርስዎም በጥያቄዎቹ ትይዩ ምላሽዎን የ"X" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | ሁልጊዜ | አብዛኛውን ጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | ጨርሶ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የመናገር ትምህርት ከማቅረቤ በፊት የትምህርቱን አላማው በግልፅ አብራራለሁ። | | | | |
| 2 | ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሊያነቃቋቸው የሚችሉ ስራዎችን እሰራለሁ። | | | | |
| 3 | ስለ መናገር የክፍል ውስጥ አቀራረብ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት እንዲያውቁ አደርጋለሁ። | | | | |
| 4 | መናገር በማስተማር ሂደት የትምህርት ይዘቱን ለማቅረብ አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን እጠቀማለሁ። | | | | |
| 5 | ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ሞዴል የመናገር ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ። | | | | |
| 6 | በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ከህይወት ገጠመኝ ጋር እንዲተሳሰሩ እና እንዲለማመዱ አደርጋለሁ። | | | | |
| 7 | በመናገር ሂደት የራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀትና ችሎታቸውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታለሁ። | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ መናገር በመማር ሂደት የተሳትፎ ጉድለት ያለባቸው፣ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ ብልሃቶችን አመቻቻለሁ። | | | | |
| 9 | የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ (አለማምዳለሁ)። | | | | |
| 10 | የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የማስተማሪያ ብልሃችን (የሚታዩ ነገሮችን ስዕል ፤ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ ) በመጠቀም እንዲለማመዱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ። | | | | |
| 11 | ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ትምህርት በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ አውድ አመቻቻለሁ። | | | | |
| 12 | የመናገር ተግባሩ ከቀረበና በዛ ላይ ከተለማመዱ በኋላ ለክፍል ሀሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ አበረታታለሁ። | | | | |
| 13 | ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ሰዎችን ጠይቀዉ ወይም ምልከታ አድርገዉ እና የተለያዩ ፅሑፎችን አንብበዉ በክፍል ዉስጥ እንዲናገሩ የሚያስችሉ ተግባራትን እሰጣቸዋል። | | | | |
| 14 | በመናገር ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር ጣልቃ በመግባት ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣጡና ስህተታቸዉን እንዲያርሙ አደርጋለሁ። | | | | |
| 15 | የመናገር ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት፣ በመናገር እያሉና ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎቹ ጥያቄ እጠይቃለሁ፤ እንዲጠያየቁም አበረታታለሁ። | | | | |
| 16 | በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶች እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አደርጋለሁ። | | | | |
| 17 | ተማሪዎቹ በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በአቻ ምጋቤ ምላሽ እርስበርስ እንዲተራረሙ አመቻቻለሁ። | | | | |
| 18 | በቀረበዉ የንግግር ትምህርት ላይ ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ። | | | | |

አባሪ 6. በመምህራን የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | ጨርሶ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የመናገር ትምህርት ከማቅረቤ በፊት የትምህርቱን አላማው በግልፅ አብራራለሁ። | 4 | 40% | 5 | 50% | 1 | 10% | - | |
| 2 | ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሊያነቃቋቸው የሚችሉ ስራዎችን እሰራለሁ። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 3 | ስለ መናገር የክፍል ውስጥ አቀራረብ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት እንዲያውቁ አደርጋለሁ። | 3 | 30% | 4 | 40% | 3 | 30% | - | |
| 4 | በትምህርቱ አቀራረብ የተማዎችን ፈጠራ በሚያበረታታ መልኩ የማስተማሪያ መሳሪያ አቀርባለሁ። | 3 | 30% | 3 | 30% | 4 | 40% | - | |
| 5 | ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ሞዴል የመናገር ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |
| 6 | በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ከህይወት ገጠመኝ ጋር እንዲተሳሰሩ እና እንዲለማመዱ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 6 | 60% | 2 | 20% | - | |
| 7 | በመናገር ሂደት የራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀትና ችሎታቸውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታለሁ። | 3 | 30% | 4 | 40% | 3 | 30% | - | |
| 8 | በክፍል ውስጥ መናገር በመማር ሂደት የተሰትፎ ጉድለት ያላባቸው፣ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ ብልሃችን አመቻቻለሁ። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |
| 9 | የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ (አለማምዳለሁ)። | 1 | 10% | 3 | 30% | 6 | 60% | - | |
| 10 | የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የማስተማሪያ ብልሃችን (የሚታዩ ነገሮችን ስዕል ፤ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ ) በመጠቀም እንዲለማመዱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 11 | ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ትምህርት በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ አውድ አመቻቻለሁ። | 2 | 20% | 5 | 50% | 3 | 30% | - | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | የመናገር ተግባሩ ከቀረበና በዛ ላይ ከተለማመዱ በኋላ ለክፍል ሀሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ አበረታታለሁ። | 3 | 30% | 4 | 40% | 3 | 30% | - | |
| 13 | ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ሰዎችን ጠይቀዉ ወይም ምልከታ አድርገዉ እና የተለያዩ ፅሑፎችን አንብበዉ በክፍል ዉስጥ እንዲናገሩ የሚያስችሉ ተግባራትን አሰጣቸዋል። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 14 | በመናገር ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር ጣልቃ በመግባት ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣጡና ስህተታቸዉን እንዲያርሙ አደርጋለሁ። | 2 | 20% | 2 | 20% | 6 | 60% | - | |
| 15 | የመናገር ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት፣ በመናገር እያሉና ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎቹ ጥያቄ እጠይቃለሁ፤ እንዲጠያየቁም አበረታታለሁ። | 3 | 30% | 1 | 10% | 6 | 60% | - | |
| 16 | በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶች እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አደርጋለሁ። | - | - | 3 | 30% | 7 | 70% | - | |
| 17 | ተማሪዎቹ በመናገር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በአቻ ምጋቤ ምላሽ እርስበርስ እንዲተራረሙ አመቻቻለሁ። | 2 | 20% | 3 | 30% | 5 | 50% | - | |
| 18 | በቀረበዉ የንግግር ትምህርት ላይ ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ። | 3 | 30% | 1 | 10% | 6 | 60% | | |